
# የተፋጠነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት ፕሮግራም

# ከዕለታት አንድ ቀን

## የተረት ጥራዝ



**ትምህርት ሚኒስቴር**

2007 ዓ.ም

# 1ኛ ሳምንት

## "ከዕለታት አንድ ቀን"

## 1ኛ ሳምንት

### ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለአንደኛ ቀን)

ልጆች ዛሬ አንዷት ልጅ እራሷን እንዴት እንደምታስተዋውቅ እንሰማለን።

ስሜ ፋጡማ ይባላል። ሰባት ዓመቴ ነው። የአባቴ ስም ኢብራሂም የእናቴ ደግሞ ሶፊያ ነው፡፡ ለወላጆቼ ሦስተኛ ልጅ ነኝ፡፡ ወንድሞቼ ዳውድና አብደላ ይባላሉ፡፡ እኔ የምወደው ሙዝ ነው፡፡ እኔን ደስ የሚለኝ ሰዎች ሲስቁ ማየት ነው፡፡ ሰማያዊ ቀለምም ያስደስተኛል፡፡ የምጠላው ደግሞ የሚደባደቡ ልጆችን ነው፡፡

የሰፈራችን ስም <u>ኢንዚ</u> የሚባል ሲሆን የምንጫወትበት ደስ የሚል አረንጓዴና ሰፊ ሜዳ አለ፡፡ ግቢያችን ውስጥ ደግሞ ትላልቅ የማንጎ ዛፎች አሉ፡፡ ፀሐይ ሲሆን ዛፎቹ ሥር ቁጭ ብሎ መጫወት ያስደስተኛል፡፡ ቤታችን የጎጆ ቤት ሆኖ ጣሪያው ሶስት ማዕዘን ግድግዳው ደግሞ አራት ማዕዘን ነው፡፡ መስኮቶቹ ክብ ሆነው ሰማያዊ ቀለም አላቸው፡፡ በሮቹ ደግሞ አራት ማዕዘን ሲሆኑ ቀይ ቀለም የተቀቡ ናቸው፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የፋጡማ አባትና እናት ስም ማን ይባላል?
2. ፋጡማ ምን ትወዳለች? የምትጠላውስ ምንድነው?
3. የፋጡማ ሰፈር ማን ይባላል?
4. የፋጡማ ቤት ምን ዓይነት ቅርጽ አለው?
5. የነፋጡማ ቤት መስኮቶች ምን ዓይነት ቅርጽ አላቸው? ቀለማቸውስ?
6. ልጆች በየተራ ስማችሁን ዕድሜያችሁን አድራሻችሁን ተናገሩ፡፡

**ምክር፡-**

ልጆች ፋጡማ እንዴት አድርጋ እራሷንና አካባቢዋን እንዳስተዋወቀች አያችሁ፡፡ ጎበዝ ናት አይደል? ልጆች እናንተም ስማችሁን የእናትና የአባታችሁን ወይም የቤተሰባችሁን ስምና አድራሻ ሁል ጊዜ ማስታወስ መቻል አለባችሁ፡፡ የሚያስደስታችሁን እና የምትጠሉትንም መናገር መቻል አለባችሁ፡፡

## 1ኛ ሳምንት

## ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለሁለተኛ ቀን)

ባለፈው ዕለት ፋጡማ ራሷን እና አድራሻዋን እንዴት እንዳስተዋወቀች ሰምተን ነበር። ዛሬ ደግሞ ስለፋጡማ ጨዋታ አጨዋወት እንሰማለን።

ፋጡማ አዘውትራ ከልጆች ጋር መጫወት ትወድ ነበር፡፡ ፋጡማ የእግር ኳስ መጫወትና መሮጥ በጣም የምትወድ ልጅ ናት፡፡ አስተማሪዋም "ፋጡማ ጎበዝ ልጅ ነሽ" እያለች ታበረታታት ነበር፡፡ ሆኖም ፋጡማ ስትጫወት በጥንቃቄ አልነበረም፡፡ ስለሆነም አንድ ቀን በኃይል ስትሮጥ ወደቀችና ቀኝ እግሯ ተሰበረ፡፡ ግንባሯ እና እጆቿ ተላላጡ፡፡ አፍንጫዋና ከንፈሮቿ ደም በደም ሆኑ፡፡ ፀጉሯ አፈር መሰለ፡፡ ደግነቱ ዓይኖቿ ምንም አልሆኑም፡፡ የእጅ ጣቶቿ ባብዛኛው መንቀሳቀስ አቆሙ፡፡ ፋጡማ ለረጅም ጊዜ እስክትድን የምትወደውን የእግር ኳስ ሳትጫወት ቀረች፡፡ የፋጡማም እግር ቀስ በቀስ እየዳነ መጣ፡፡ ከዚያ በኋላ ፋጡማ እግር ኳስን በጥንቃቄ መጫወት ጀመረች፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የተነበበው ተረት ስለምን ነበር?
2. ፋጡማን የምታበረታታት ማን ናት? ምን አለቻት?
3. ፋጡማ ለረጅም ጊዜ እግር ኳስ ሳትጫወት የቀረችው ምን ሆና ነው ?
4. የትኛው የአካል ክፍሏ ከባድ ጉዳት ደረሰበት?
5. በጥንቃቄ ካልተጫወትን ምን እንሆናለን?

**ምክር፡-**አያችሁ ልጆች ስትጫወቱ በጥንቃቄ መሆን አለበት፡፡ አለበለዚያ በአካል ክፍሎቻችሁ ላይ ከባድ ጉዳት ሊያጋጥማችሁ ይችላል፡፡ እጆቻችሁ ወይም እግሮቻችሁ ሊሰበሩ ይችላሉ፡፡

## 1ኛ ሳምንት

### ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለሦስተኛ ቀን)

ባለፈው ዕለት ፋጡማ የእግር ኳስ ስትጫወት በጥንቃቄ ባለመጫወትዋ አደጋ እንደደረሰባት፡ ከዚያም በኋላ ድና በጥንቃቄ መጫወት እንደጀመረች ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ፋጡማ ምን እንዳጋጠማት እንሰማለን፡፡

አንድ ቀን የፋጡማ እናት ወ/ሮ ሶፊያ ለፋጡማ ሙዝና ብርቱካን ለመግዛት ወደ ገበያ ሄዱ፡፡ ቅርጫት ሙሉ ሙዝና ብርቱካን ገዝተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ እቤታቸውም እንደደረሱ የገዙትን ሙዝና ብርቱካን ጓዳ በሚገኘው ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው አረፍ ሊሉ ወደ መኝታ ቤት ሄዱ፡፡ ፋጡማ ከት/ቤት ስትመጣም እናቷ "ጓዳ ሂጂና የገዛሁልሽን ሙዝና ብርቱካን አምጪ፣ እጅሽንም ታጥበሽ ትበያለሽ" አሏት፡፡ እሷም ደስ ብሏት ወደ ጓዳ ሄደች፡፡ እጓዳ ስትደርስ ብርቱካኑ መሬት ላይ ወዳድቆ ነበር፡፡ ሙዙ ግን አልነበረም፡፡ በመስኮት ወደ ውጭ ስትመለከትም አንዲት ጦጣ ዛፍ ላይ ቁጭ ብላ ሙዝ ስትበላ አየች፡፡ ፋጡማም ጮክ ብላ አለቀሰች፡፡ እናቷም ለቅሶዋን ሰምተው ወደ ጓዳ መጡ፡፡ ፋጡማንም "አይዞሽ በቃ አታልቅሺ፤ አሁን ብርቱካኑን እጠቢና ብዪ፤ ሙዙን ሌላ ጊዜ እገዛልሻለሁ" አሏት፡፡ "እኔም ጦጣዋ ሁለተኛ ገብታ እንዳትሰርቅ መስኮቱን መዝጋት አልረሳም" አሉ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የፋጡማ እናት ወደ ገበያ ለምን ሄዱ?
2. ወ/ሮ ሶፊያ ከገበያ ሲመለሱ ምን አደረጉ?
3. ሙዝና ብርቱካን ምን ዓይነት ቀለም አላቸው?
4. ፋጡማ ለምን አለቀሰች?
5. የፋጡማ እናት ለምን ወደ መኝታ ቤት ሄዱ ?
6. ጦጣዋ ገብታ እንዳትሰርቅ ወ/ሮ ሶፊያ ምን ማድረግ ነበረባቸው?

**ምክር፡-** ስርቆት በጣም መጥፎ ነገር ነው፡፡

## ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለአራተኛ ቀን)

ባለፈው ዕለት እነፋጡማ ቤት ስለተከሰተው ነገር ሰምተን ነበር፡፡ ምን እንደነበር ታስታውሳላችሁ? እስቲ ማን አለ የሚነግረን? ዛሬ ደግሞ ፋጡማ ቤት ውስጥ ስትጫወት በነበረ ጊዜ ምን እንዳጋጠማት እንሰማለን፡፡

አንድ ቀን ፋጡማ ከትምህርት ቤት መጥታ በቤት ውስጥ ስትጫወት አንድ ትንሽ ጠርሙስ አየች፡፡ ቀስ ብላ ጠርሙሱን ከፍታ ስታሸተው መድሃኒት ስለነበር በጣም ይሸት ነበር፡፡ ቆይ እስኪ "እስኪ ምን ምን ይላል?" አለችና ፈሳሹን ትንሽ ቀመስ አደረገች፡፡ ቆየት ብሎ ሆዷን በጣም አመማት፡፡እናቷም ቶሎ ብለው ወደ ሀኪም ቤት ወሰዷት፡፡ ሀኪሙም መድሃኒት ከሰጣት በኋላ ሁለተኛ ወላጆቿ ያስቀመጡትን መንካት እንደሌለባት ሀኪሙ መከራት፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ፋጡማ ከትምህርት ቤት እንደተመለሰች ምን እያደረገች ነበር?
2. ፋጡማ እየተጫወተች ሳለች ምን አገኘች ?
3. ፋጡማ ያገኘችውን ነገር ምን አደረገችው?
4. የፋጡማ እናት ፋጡማን ለምን ወደ ሀኪም ቤት ወሰዷት?
5. ፋጡማ ጠርሙሱን ስታገኝ ምን ማድረግ ነበረባት?ለምን?

**ምክር፡-**ኢያችሁ 'ልጆች ወላጆች ያስቀመጡትን ነገር ሳታስፈቅዱ መንካት የለባችሁም፡፡

## 1ኛ ሳምንት

## ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለአምስተኛ ቀን)

ባለፈው ዕለት ፋጡማ ቤት ውስጥ ስትጫወት በነበረ ጊዜ ስላጋጠማት ነገር ሰምተን ነበር፡፡ ምን እንደነበር ታስታውሳላችሁ? እስቲ ማን አለ የሚነግረን? ዛሬ ደግሞ ፋጡማ ምግብዋን ስትመገብ ምን እንደምታደርግ እንሰማለን፡፡

የፋጡማ እናት ወ/ሮ ሶፊያ ፋጡማ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ ሁል ጊዜ ለምሳዋ የሚሆን ምግብና ውሃ ያስይዟታል፡፡ ምግቧንም በሰዓቱ እጇን ታጥባ በደንብ እንድትመገብ ይመክሯታል፡፡ ባትመገብ ግን በቀላሉ በበሽታ እንደምትያዝ ይነግሯታል፡፡ ፋጡማም የእናቷን ምክር በመስማት የተሰጣትን ምግብ እጇን ታጥባ ትበላለች፡፡ ንጹህ ውሃም ትጠጣለች፡፡ ከጨረሰችም በኋላ እጇን በመታጠብ የምሳ ዕቃዋን በቦርሳዋ ከታ ወደቤት ትሄዳለች፡፡ የፋጡማ እናትም "ጎበዝ የኔ ልጅ ምግብሽን በሰዓቱ በመመገብሽ ጤናማ ሆነሽ ትምህርትሽን በጥሩ ሁኔታ ለመማር ችለሻል" አሏት፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የፋጡማ እናት ፋጡማ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ ምን ያስይዟታል?
2. ፋጡማ ምግቧን ከመመገቧ በፊት ምን ታደርጋለች?
3. የፋጡማ እናት ፋጡማን ምን ብለው መከሯት?
4. ለሰውነታችን አስፈላጊ የሆኑት ምንድን ናቸው?

**ምክር፡-**ልጆች ለሰውነታችን ምግብና ውሃ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ስለሆነም እኛም እንደ ፋጡማ በደንብ መመገብ አለብን፡፡

## 2ኛ ሳምንት

# "ከዕለታት አንድ ቀን"

## 2ኛ ሳምንት

### ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለአንደኛ ቀን)

ልጆች ባለፈው ሳምንት ስለፋጡማ ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በቤታቸው ስለነበረው ሠርግ እንሰማለን፡፡

ዛሬ የፋጡማን ቤተሰብ ደስ ብሎታል፡፡ የፋጡማ አጎት ሰልማን የሚያገባበት ዕለት ነው፡፡ ሰልማን ቀጭንና ረጅም ነው፡፡ የሠርጉ ድግስ የተዘጋጀው እነፋጡማ ቤት ስለሆነ ሁሉም የቤተሰብ አባል ተደስተዋል፡፡ የፋጡማ አያቶች ለሠርጉ የሚያስፈልገውን እህል ጭነው ከገጠር መጥተዋል፡፡ ሠርጉ በደመቀ ሁኔታ እንዲከናወንም እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሥራ ድርሻ ተሰጥቶታል፡፡ የፋጡማ ወንድም አብደላም ለሠርጉ የሚያገለገሉ ዕቃዎችን የማጠብ እንዲሁም ግቢውንና የሠርጉን ዳስ የማስዋብ ሥራ በጠዋት ተነስቶ በደስታ አጠናቋል፡፡ አባቱም ዝግጅቱን ከተመለከቱ በኋላ አብደላን "እንዲህ ነው የኔ ልጅ! በጣም ጎበዝ ነህ ፣ጥሩ ሥራ ሠርተሃል፣ አመሰግንሃለሁ" ብለው አበረታቱት፡፡

በሠርጉ ላይ የተዘጋጀው ምግብና መጠጥም ቀርቦ በደስታ ሲበላ፣ ሲጠጣና ሲጨፈር አመሸ፡፡ በተለይ አብደላ እምቢልታ የመንፋት ልዩ ችሎታውን በማሳየቱና ከአክስቱ ጋር ባሳየው የጭፈራ ፉክክር ሁሉም አጨበጨበለት፡፡ በመጨረሻም ሙሽሮቹን በመካከል አድርገው የቤተሰቡ አባላት በጠቅላላ የሚታዩበት ፎቶ ተነሱ፡፡ ሁሉም የቤተሰቡ አባላት ደስተኞች ነበሩ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የፋጡማን ቤተሰብ ለምን ደስ አላቸው?
2. ከእናንተ ቤተሰብ ቀጭን ማን ነው? ረዥሙስ?
3. የነፋጡማ አያቶች ምን ይዘው መጡ?
4. በሰርጉ ዕለት የአብደላ የሥራ ድርሻ ምን ነበር?
5. ለአብደላ ሁሉም ያጨበጨቡለት ለምንድን ነው?
6. በመጨረሻ የነፋጡማ ቤተሰብ አባላት ምን አደረጉ?

**ምክር**

አያችሁ ልጆች ቤተሰብን የሚያስደስት ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

## 2ኛ ሳምንት

### ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለሁለተኛ ቀን)

ልጆች ባለፈው እነ ፋጡማ ቤት ስለነበረው የቀጭኑ ሰልማን ሠርግ ስነሥርዓት ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለፋጡማ ቤተሰቦች መረዳዳት እንሰማለን፡፡

የፋጡማ ቤተሰቦች ነጋዴዎች ናቸው፡፡ የፍራፍሬ ሱቅ አላቸው፡፡ የፋጡማ እናትና አባት በጥዋት ተነስተው ከልጆቻቸው ጋር ቁርስ በልተው ለፋጡማ፣ ለዳውድ እና ለአብደላ የምሳ ዕቃዎቻቸውን በየቦርሳቸው አስይዘው በተለይ ፋጡማን ወደ ትምህርት ቤት ካደረሷት በኋላ ቀጥታ ወደ ሱቃቸው በመሄድ የንግድ ሥራቸውን ሲያከናወኑ ይውላሉ፡፡ አብደላና ዳውድም ከት/ቤት በፊት አራት ማዕዘን ያለውን የፍራፍሬ ሳጥን በመደርደር ያግዛሉ፡፡ ከት/ቤት በኋላም ወደሱቅ በመሄድ የተበላሸውን ፍራፍሬ በክቡ ቅርጫት ያኖራሉ፡፡ ፋጡማም በእረፍት ቀኗ አንዳንድ ጊዜ ሱቅ በመሄድ እናትና አባቷን ትረዳ ነበር፡፡ የፋጡማ እናትና አባት በቤተሰቡ መረዳዳት በጣም ይደሰቱ ነበር፡፡ አባትየው አቶ ኢብራሂም ቤተሰቡን ሲመክሩ "ሁልጊዜ ደስተኛ ለመሆን ከፈለጋችሁ ልክ እንደ ሠርጉ ዕለት ሥራን ተከፋፍላችሁና ተባብራችሁ ሥሩ" ይላሉ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የፋጡማ ወላጆች በጠዋት ተነስተው ምን ያደርጋሉ?
2. ፋጡማን ወላጆቿ ምን ይሏታል? ለምን?
3. ከት/ቤት በፊት የፋጡማ ወንድሞች ተግባር ምንድን ነው?
4. የፋጡማ ወላጆች በምን ሥራ ላይ ተሰማርተዋል?
5. የነፋጡማ ቤተሰብ ለምን ደስተኛ የሆኑ ይመስላችኋል?

**ምክር**

አያችሁ ልጆች እኛም በእረፍት ቀናችን እናትና አባታችንን መርዳት አለብን፡፡ ቤተሰቦቻችን በኛ በልጆቻቸው ደስ ይላቸዋል፡፡

## 2ኛ ሳምንት

## ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለሦስተኛ ቀን)

ልጆች ባለፈው በእነ ፋጡማ ቤት ስለነበረው መረዳዳት ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በአጠቃላይ ስለፋጡማ ቤተዘመዶች አኗኗር እንሰማለን፡፡

በእነ አቶ ኢብራሂም ቤት ሌሎችም ቤተዘመዶች አብረዋቸው ይኖሩ ነበር፡፡ እነዚህም ባለፈው በሠርግ ያገባው ቀጭኑ የአቶ ኢብራሂም ወንድም ሰልማን፣ የወ/ሮ ዘሀራ እህት ሀቢባ፣ የአክስታቸው ልጅ የሆነው ሬድዋን እና የአጎታቸው ልጅ ዑስማን ናቸው። የነፋጡማ አያቶችም አልፎ አልፎ ከገጠር ለሰርግ መጥተው ከነፋጡማ ጋር አብረው መኖር ቀጥለዋል። ሁልጊዜም በነፋጡማ ቤት ቤተዘመዶች ይኖራሉ።

ታድያ በአንድ ቤት ውስጥ አብረው ስለሚኖሩ የአቶ ኢብራሂም ቤተሰብ ቁጥር ብዙ ይሁን እንጂ ሁሉም በአንድነት በመኖራቸው ደስተኞች ናቸው፡፡ ልጆቻቸው እና አብረዋቸው የሚኖሩት ቤተዘመዶቻቸው እነ አቶ ኢብራሂምን በሥራ ይረዷቸው ነበር፡፡ ሀቢባ የአቶ ኢብራሂም ሱቅ ገንዘብ ተቀባይ ስትሆን ሰልማን ለሱቁ የሚሆን ዕቃ ያቀርባል። ሬድዋንና ዑስማን ደግሞ ከባድ ዕቃዎችን ከመደርደሪያ በማወረድና ጋሪ ላይ በመጫን ያግዛሉ፡፡ እነ አቶ ኢብራሂም ደግሞ ለእነሱ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ እንደ ምግብና ልብስ ያሉትን እንዲያገኙ ያደርጉ ነበር፡፡

### ጥያቄዎች

1. የቤተሰብ አባላት የሚባሉት እነማን ናቸው?
2. በነ አቶ ኢብራሂም ቤተሰብ ውስጥ አብረው የሚኖሩ ሰዎች እነማን ናቸው?
3. በእናንተስ ቤተሰብ ውስጥ እነማን አብረዋችሁ ይኖራሉ?
4. የእናንተን ቤተሰብና የዘመዶቻችሁን ስም ታውቃላችሁ?
5. የአቶ ኢብራሂም የቤተሰብ አባላት በቤት ውስጥ ምን ምን ሥራ ይሰራሉ?
6. የቤተሰብ አባላት ተረዳድተው የሚኖሩት ለምን ይመስላችኋል?

**ምክር**

አያችሁ ልጆች አንዳንድ ጊዜ ዘመድ ወይም ሌሎች የምንረዳቸው ሰዎች አብረውን ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ተረዳድቶ መኖር መልካም ነው፡፡ ቤተሰቡን ደስተኛ ያደርጋል፡፡

## 2ኛ ሳምንት

## ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለአራተኛ ቀን)

ልጆች ባለፈው በእነ ፋጡማ ቤት የፋጡማ ቤተዘመዶች አኗኗር ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለነፋጡማ ግቢ እና መኖሪያ ቤት ሁኔታ እንሰማለን፡፡

የነፋጡማ ቤት ሰፊ ነው፡፡ በውስጡም ልዩ ልዩ ክፍሎች አሉት፡፡ ክፍሎችም የእንግዳ መቀበያ ክፍል (ሣሎን)፣ የመኝታ ክፍሎች፣ የማብሰያ ክፍል እና መፀዳጃ ቤት ይባላሉ፡፡ በእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ሰፊ ምንጣፍ እንዲሁም በርካታ መቀመጫዎች ይገኛሉ፡፡ ግድግዳዎቹ ቢጫ ቀለም ተቀብተው የተለያዩ ፎቶግራፎችም ተሰቅለው ይታያሉ፡፡ ከሁሉም ትልቁ ፎቶግራፍ በሰልማን የሠርግ ዕለት የተነሱት የቤተሰብ ፎቶግራፍ ነው፡፡ የቤተሰቡም አባላት ዘወትር ጠዋት የየራሳቸውን መኝታ በማንጠፍ መኝታ ክፍሎቻቸውን ያጸዳሉ፡፡ በማብሰያ ክፍላቸው ምግባቸውን ካዘጋጁ በኋላ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ተሰባስበው ቁርሳቸውን እየበሉ ስለዕለቱ ሥራዎቻቸው ይወያያሉ፡፡

መጸዳጃ ቤታቸው ጠባብ ቢሆንም በጽዳት ተይዟል፡፡ ሰማያዊ ቀለም ተቀብቷል፡፡ ውስጡን ዘወትር ጠዋት በየተራ ያጥቡታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መጸዳጃ ቤት ገብቶ የተጠቀመ የቤተሰቡ አባል በተጠቀመ ቁጥር ውሃ የማፍሰስ ግዴታ አለበት፡፡ ግቢያቸውም ያማረና ሰፊ ነው፡፡ በውስጡም አበቦች፣ ዛፎችና ፍራፍሬዎች አሉ፡፡ ፋጡማና ወንድሞቿ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ አብዛኛውን ጊዜ አትክልቶቹን ይንከባከባሉ በግቢው ውስጥም ይጫወታሉ፡፡

### ጥያቄዎች

1. በነፋጡማ ቤት የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ምን ዓይነት ቁሳቁሶች አሉ?
2. የእናንተስ ቤት ልጆች ምን ዓይነት ነው? የተለያዩ ክፍሎች አሉት? ግቢያችሁስ ለጫዋታ ያመቻልን?
3. በነፋጡማ ቤት የመኝታ ክፍሎችን ማን ያጸዳል? እናንተስ ቤት?
4. የነፋጡማ መጸዳጃ ቤት ጽዳት የሚጠበቀው እንዴት ነው?
5. መጸዳጃ ቤቱ ንጹህ ባይሆን ምን ይሆናል?
6. እነፋጡማ በግቢያቸው ያሉ አትክልቶችን ለምን የሚንከባከቡ ይመስላችኋል?

**ምክር**

አያችሁ ልጆች የቤታችሁን ክፍሎችና ግቢያችሁን ማስዋብና ለኑሮ አመቺ እንዲሆን ማድረግ አለባችሁ፡፡

## 2ኛ ሳምንት

## ከዕለታት አንድ ቀን (የተረት ጊዜ ለአምስተኛ ቀን)

ልጆች ባለፈው ስለነፋጡማ መኖሪያ ቤት እና ግቢ ሁኔታ ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለ ፋጡማ ባህሪ እንሰማለን፡፡

የፋጡማ ታላቅ ወንድም ዳውድ ፋጡማ ዘወትር የቤት ሥራ ስትሰራ እንዴት መስራት እንዳለባት ያሳያታል፡፡ፋጡማ በዚህ ሁኔታ ስለምትደሰት ሁልጊዜ ወንድሟን ታመሰግናለች፡፡ አመሰግናለሁ ዳውድዬ በትምህርቴ ጎበዝ እንድሆን ስለረዳኸኝ በጣም ደስ ይለኛል ትላለች፡፡ ፋጡማ ጎበዝ ልጅ ናት፡፡ ፋጡማ መምህሯ እንድትፈቅድላት ስትፈልግ እባክሽ መምህርት ፍቀጅልኝ ማለትን ለምዳለች፡፡ ስትፈቅድላትም "አመሰግናለሁ መምህርት" ትላለች፡፡ ጓደኞቿም አንድ ነገር እንዲያውሷት ስትፈልግ እባክሽ ወይም እባክህ በማለት ትጠይቃለች፡፡ በኋላም "አመሰግናለሁ" በማለት ትመልሳለች፡፡

ፋጡማ ከቤተሰቧም ሆነ ከጓደኞቿ ጋር ጥሩ ግንኙነት አላት፡፡ ጓደኞቿን፣ ታላላቆቿን እና ቤተሰቧን ታከብራለች፡፡ የቤተሰቧን ምክር ታዳምጣለች፡፡ ተግባራዊ ለማድረግም ትጥራለች፡፡ ታላላቆቿ ሲናገሩ በጥሞና ታዳምጣለች፡፡ ለመናገር አትቸኩልም፡፡ በንግግር ወቅትም ትህትናን ታሳያለች፡፡ ከጓደኞቿም ሆነ ከወንድሞቿ ጋር በምትጫወትበትም ወቅት ካጠፋች ይቅርታ ትጠይቃለች፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ፋጡማ ምን ዓይነት ባህሪ ያላት ልጅ ናት?
2. ጥፋት ያጠፋ ልጅ ቤተሰቡን ለመታረቅ በመጀመሪያ ምን ማድረግ አለበት?
3. መልካም ነገር ለሚያደርጉላችሁ ምን ትላላችሁ?
4. ፋጡማ ከታላላቆቿ ጋር ያላት ግንኙነት ምን ይመስላል?
5. እናንተስ ከጓደኞቻችሁ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን ይመስላል?

**ምክር**

አያችሁ ልጆች ስታጠፉ ይቅርታ መጠየቅ አለባችሁ፡፡ መልካም ነገር ለሚያደርጉላችሁ ሰዎች ደግሞ ማመስገን ተገቢ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚያስፈልጉንን ነገሮች መጠየቅ እንፈልግ ይሆናል፡፡ በዚያን ጊዜ ደግሞ እባክሽ/ህ/ በማለት መጠየቅ አለብን፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ባህርያት ሊኖረን ይገባል፡፡

# 3ኛ ሳምንት

## "ከዕለታት አንድ ቀን"

## 3ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአንደኛው ቀን)

ባለፈው ሳምንት ስለፋጡማ የቤተሰብ እና ስለ መኖሪያቸው ሰምተን ነበር፡፡ እስቲ ማን አለ ስለአለፈው ሣምንት የሰማውን የሚነግረን፡፡ በጣም ጥሩ ሁላችሁም ጥሩ አስተውሳችኋል፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለ እጅ መታጠብ እንሰማለን፡፡

ፋጡማ ትንሽ ልጅ ናት፡፡ ሁልጊዜ አስተማሪዋ ፋጡማንና ጓደኞቿን እነ ሰዓዳን፣ አሊን፣ ነኢማን፣ ሩቂያን በሳሙናና በውሃ ሳትታጠቡ ምግብ መመገብ የለባችሁም በማለት ትመክራቸዋለች፡፡ ከበላችሁም በኋላና ከመፀዳጃ ቤትም ስትመለሱ እጃችሁን በደንብ አድርጋችሁ በሳሙናና በውሃ ታጠቡ እያለች መምህራቸው ታስተምራቸዋለች፡፡ ነገር ግን ከፋጡማ ጓደኞች አንዱ የሆነው አሊ ሁል ግዜ ምግብ ሲበላና ከመፀዳጃ ቤት ሲመለስ እጁን መታጠብ ይረሣ ነበር፡፡ በመሆኑም ብዙ ጊዜ ሆዱን ያመዋል፡፡ አንድ ቀን የአሊ እናት ወ/ሮ ናዲያ አሊን ይዘው ወደ ሐኪም ቤት ሄዱ ሐኪሙም አሊ የታመመው ሆዱ ውስጥ በሽታ አምጭ ጀርሞች ገብቶበት ነው አለ፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ እጁን ሳይታጠብ ምግቡን ስለሚበላና ከመፀዳጃ ቤት መልስም ስለማይታጠብ ነው አለ፡፡ ሐኪሙ፣ እናቱ እና ጓደኞቹ አሊ የመምህርቷን ምክር ባለመስማቱ እንደታመመ ተረዱ፡፡ አሊ ሐኪሙ ያዘዘለትን መድሀኒት በትክክል ወሰደ፡፡ ከዚያን ቀን በኋላ አሊ እጁን መታጠብ ተለማመደ፡፡ ሆዱንም ሳይታመም በደስታ መኖር ጀመረ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የፋጡማ ጓደኞች እነማን ናቸው?
2. የነፋጡማ አስተማሪ ምን እያለች ታስተምራቸዋለች?
3. አሊ ምን ሆኖ ነው የታመመው?
4. አሊ መጨረሻ ላይ ምን አደረገ?
5. እጃችንን መቼና እንዴት መታጠብ አለብን? ለምን?
6. እጃችን ባንታጠብ ምን እንሆናለን?

**ምክር፡** አያችሁ ልጆች እናንተም ሁልግዜ ከምግብ በፊትና በኋላ እንዲሁም ከመፀዳጃ ቤት ስትመለሱ እጃችሁን በውሃና በሣሙና መታጠብ አለባችሁ፡፡ ይህንን ማድረግ ጤናማና ደስተኞች እንድትሆኑ ያደርጋችኋል፡፡

## 3ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሁለተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የፋጡማ ጓደኛ የሆነው “አሊ” ሁልጊዜ እጁን ማይታጠብ ስለሚበላ ታሞ ሀኪም ዘንድ እንደ ሄደና ታክሞ ከበሽታው እንደዳነ ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ነኢማ ስለምትባለው ሌላዋ የፋጡማ ጓደኛ ንጽህና አጠባበቅ እንሰማለን፡፡

ከፋጡማ ጋር በአፀደ ሕፃናት ውስጥ አብረዋት ከሚማሩት ጓደኞቿ አንዷ ነኢማ ትባላለች፡፡ ነኢማ ወደ ትምህርት ቤት ስትመጣ ፊቷን ታጥባ ፀጉሯን አበጥራና ቦርሳዋን ይዛ ትመጣለች፡፡ ነኢማ ፊቷን በውሃና በሳሙና ሁልግዜ ስለምትታጠብ አይኖቿና አፍንጫዋ ሁል ጊዜ ንፁህ ናቸው፡፡ ፀጉሯንም ካበጠረች በኋላ በሪቫንዋ ታስረዋለች፡፡ ከምግብ በኋላ አፏን ትጉመጠመጣለች፡፡ ጠዋት ጠዋትም ጥርሷን ትፍቃለች፡፡ በመሆኑም የነኢማ ጥርስ ሁልግዜ ነጭ ነበር፡፡ በተጨማሪ በጥርሶቿ መሃከል ምንም የምግብ ቁራጮች ስለማይቀሩ የጥርስ በሽታ ይዟት አያውቅም፡፡ ነኢማ ሁል ጊዜ ንፁህ ናት፡፡ ስለዚህ ፋጡማና ሌሎች ጓደኞቿ በጣም ይወዷታል፡፡ አንድ ቀን አስተማሪዋ ስለ ግል ንጽህና ስታስተምር “ልክ እንደ ነኢማ አይናችሁንና አፍንጫችሁን ማጽዳት፣ ፀጉራችሁንም እየታጠባችሁ ማበጠር፣ ጥርሳችሁን መፋቅ፣ ከዚያ ልክ እንደ ነኢማ ንፁህ፣ ቆንጆ እና ጤናማ መሆን” አለባችሁ - ብላ ስትናገር ነኢማ ደስ አላት፡፡

### ጥያቄዎች

1. ነኢማ ፀጉሯን እንዴት ትይዛለች?
2. አስተማሪዋ ስለ ነኢማ ምን አለች?
3. ነኢማ ንጽህናዋን ለመጠበቅ የምትጠቀምባቸው መሣሪያዎች ምንድናቸው ?
4. ንጽህና ለምን ይጠቅማል?

**ምክር፡** ስለዚህ ልጆች ጤናማና ቆንጆ እንድትሆኑ ሁልግዜ ራሳችሁን በተለይም ደግሞ አይናችሁን፣ አፍንጫችሁን፣ ፀጉራችሁን፣ ጥርሳችሁን በንጽህና መያዝ አለባችሁ፡፡

## 3ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሦስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የፋጡማ ጓደኛ የሆነችው ነኢማ ፊቷን፣ አይኗን፣ አፍንጫዋንና ጥርስዋን ሁልጊዜ እንዴት በንጽህና እንደምትይዝ ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ከፋጡማ ጓደኞች አንዷ ስለሆነችው ሩቂያ መጽሐፍት አያያዝ እንሰማለን፡፡

ከፋጡማ ጓደኞች አንዷ ሩቅያ ትባላለች፡፡ ሩቂያ ጎበዝ ተማሪ ነች፡፡ ሁል ግዜ ደብተሯንና መጽሐፍቷን ይዛ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች፡፡ በትምህርት ቤትም መጽሐፎቿን በሥነ-ሥርዓትና በንጽህና ትጠብቃለች፡፡ አስተማሪዋ መጽሐፍት አውጡ ስትል በጥንቃቄ ከቦርሳዋ አውጥታ ከቀኝ ወደ ግራ በመግለጥ የታዘዘችውን የመጽሐፉን ገፅ ታወጣለች፡፡ ሩቅያ በትምህርት ቤት ብቻ ሣይሆን በቤቷም መጽሐፍ ታነባለች፡፡ ለማንበብ ስትዘጋጅ ሁልጊዜ አስቀድማ እጇን ትታጠብና በፎጣ ታደርቃለች፡፡ ከዚያም በጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብላ ታነባለች፡፡ የቤት ሥራዎቿንም በዚህ ዓይነት ትሰራለች፡፡ ከጨረሰችም በኋላ ቦርሳዋ ውስጥ ታስቀምጣለች፡፡ የሩቂያ መጽሐፍ ሁል ግዜ ንፁህና ያልተቀዳደዱ ናቸው፡፡

### ጥያቄዎች

1. ሩቂያ መጽሐፎቿን እንዴት ነው የምትይዘው?
2. መጽሐፍትን በጥንቃቄ መያዝ ለምን ይጠቅማል?
3. መጽሐፍትን በጥንቃቄ ለመያዝ ምን ማድረግ ይገባል?

**ምክር፡** አያችሁ ልጆች የሩቂያ መጽሐፍት ሁል ጊዜ ንፁህና ያልተቀዳደዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ልጆች መጽሐፍትን በጥንቃቄ ስንይዝ ሳይበላሹና ሳይቀዳደዱ ለረዥም ጊዜ ልንጠቀም እንችላለን፡፡ እናንተም እንደ ሩቂያ መጽሐፎቻችሁን በጥንቃቄ መያዝ ይኖርባችኋል፡፡

## 3ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአራተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት ከፋጡማ ጓደኞች አንዷ ስለሆነችው ሩቂያ መጽሐፍት አያያዝ ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለ የአካባቢ ንጽህና አስፈላጊነት ተረት እንሰማለን፡፡

ከእለታት አንድ ቀን በአንድ መንደር ውስጥ አብረው የሚኖሩ ዝሆን፣ አንበሳ፣ ዝንጀሮ፣ አህያ፣ ውሻ፣ድመት፣ ወፍ ነበሩ፡፡ በጋራም ትርዒት በማሳየት ሰዎችን ያዝናናሉ፡፡ አንድ ቀን ተሰበሰቡና ትርዒት ካሳየን በኃላ ገላችንንና በየተራም አካባቢያችንን ማጽዳት አለብን ብለው ወሰኑ፡፡ ትርዒት አሳይተው እንደጨረሱ አንበሣ ፣ አህያ ፣ ድመት ፣ ውሻ አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ፤ ዝሆን፣ ውፍ፣ ዝንጀሮ እና ሁለተኛዋ አንበሣ ገላቸውን እንዲታጠቡ በውሳኔያቸው መሰረትም አንበሳ ረጅም መጥረጊያ በመያዝ፣ አህያ አጭር መጥረጊያ በመያዝ፣ ድመት ጨርቅ በመያዝ ፣ ውሻ ውሀ በማቀበል ማጽዳት ጀመሩ፡፡ አጽድተው ከጨረሱም በኃላ ቆሻሻውን በቆሻሻ መጣያ በጥንቃቄ አጠራቀሙት፡፡

ሌሎች እንስሳት ዝሆን፣ ውፍ፣ ዝንጀሮ እና ሁለተኛዋ አንበሣ ወደ ወንዝ በመሄድ ገላቸውን ታጠቡ፡፡ ከዛም በኃላ የግልና የአካባቢያቸውን ንጽህና ጠብቀው በጋራ ትርዒት እያሳዩ ኖሩ፡፡

<u>**ጥያቄዎች**</u>

1. ለአካባቢ ንጽህና የሚያገለግሉ ቁሣቁሶች ምንድናቸው?
2. የግል ንጽሕናችንን ጠብቀን የአካባቢያችንን ንጽሕና ባንጠብቅ ምን ችግር ይፈጠራል?

**ምክር፡** ልጆች ጤናማና ቆንጆ እንድትሆኑ ሁልግዜ ራሳችሁን እና አካባቢያችሁን በንጽህና መያዝ አለባችሁ፡፡

## 3ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአምስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት ስለ አካባቢ ንጽህና አስፈላጊነት ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ የነፋጡማ ሌላው ጓደኛቸው አብዲ የተለያዩ መጫወቻዎችን በወረቀት እንዴት እንደሚሠራ እንሰማለን፡፡

ከፋጡማ የአፀደ ሕፃናት ጓደኞቿ አንዱ የጎረቤት ልጅ የሆነው አብዲ ይባላል፡፡ አብዲ መጫወት በጣም ይወዳል፡፡ በተጨማሪም አውሮፕላኖችን ከወረቀት መሥራት ይችላል፡፡ አውሮፕላኖችን ሰርቶ ወደ ላይ ሲወረውራቸው በአየር ላይ ይንሳፈፋሉ፡፡ ፋጡማና ሌሎች ጓደኞቹ ከአብዲ ጋር መጫወት በጣም ይወዳሉ፡፡ በወረቀት የአውሮፕላን ቅርጽ ሠርተውና በክር አስረው በመሮጥ በአየር ላይ እንዴት እንደሚንሳፈፉ እያዩ ይደሰታሉ፡፡ አብዲ ወረቀት በማጣጠፍ የተለያዩ ቅርፆች መሥራት እንዴት እንደሚቻል ለሁሉም የሰፈር ልጆች አለማመዳቸው፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ጨዋታ የሚወደው የፋጡማ ጓደኛ ማን ይባላል?
2. እነ ፋጡማ የሚጫወቱት ጨዋታ ምን ይባላል?
3. እነ ፋጡማ የሚጫወቱት ጨዋታ ከምን የተሰራ ነው?

**ምክር፡** እነ አብዲ ፋጡማና ሌሎች ልጆች ይህንን ጨዋታ አዘውትረው ይጫወታሉ እናንተም እንደ አብዲ እንደ ፋጡማና ጓደኛቸው በወረቀት አውሮኘላን እየሠራችሁ ተጫወቱ፡፡

# 4ኛ ሳምንት

## "ከዕለታት አንድ ቀን"

## 4ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአንደኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ሳምንት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች፤ ልክ ናችሁ። ባለፈው ሳምንት ስለ ግልና አካባቢ ንጽህና እንዲሁም በወረቀት ስለሚሰራ ጨዋታ ነበር የተማራችሁት። ዛሬ ደግሞ ስለ አንድ የአጸደ ህጻናት ተማሪ የቀን ወሎ እንሰማለን።

አህመድ የተባለ አንድ የአፀደ ሕፃናት ተማሪ ነበር፡፡ አህመድ በጠዋት ተነስቶ ፊቱን ታጥቦና ቁርሱን በልቶ ጥርሱን ፍቆ ወደ ት/ቤት ይሄዳል፡፡ የት/ቤቱንም ስም በሚገባ መናገር በመቻሉ ችግር ገጥሞት አያውቅም፡፡ የት/ቤቱን አቅጣጫና የሚገኝበትን ቦታ አስተውሎ በማየቱ ማንንም ሳያስቸግር ጠዋት ተነስቶ ወደ ት/ቤት ይሄድ ነበር፡፡ ከሰዓት በኋላም ትምህርት ሲያበቃ ራሱን ችሎ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ እቤት ከደረሰ በኋላም ትንሽ ተጫወቶና ከታላቅ ወንድሙ ጋር ንባብን ተለማምዶ የቤት ሥራውን ሰርቶ ሲመሽ እራቱን በልቶ እግሩን ታጥቦ ቶሎ ብሎ ይተኛል፡፡ ወላጆቹም ጎበዝ የኛ ልጅ እያሉ ያበረታቱት ነበር።

**ጥያቄዎች**

1. አህመድ በጠዋት ተነስቶ ምን ያደርጋል?
2. አህመድ ወደ ት/ቤት ከማን ጋር ይሄዳል?
3. አህመድ ወደ ት/ቤት ሲሄድ ችግር ገጥሞት የማያውቀው ለምንድን ነው?
4. ከሰዓት በኋላ ሲሆን አህመድ ምን ያደርጋል?
5. አህመድ ቤት ሲደርስ ምን ይሰራል?
6. አህመድ ምን ጊዜ ወደ መኝታው ይሄዳል?

**ምክር፡**

አያችሁ ልጆች እናንተም የት/ቤታችሁን ስም ማወቅ አቅጣጫና የሚገኝበትን ቦታ አስተውላችሁ ማየት አለባችሁ፡፡

## 4ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሁለተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን እንደነበር የሚያስታውስ አለ? አዎ! ልክ ነው። የአህመድን የቀን ውሎ ነበር። ልጆች ዛሬ ደግሞ ስለ አህመድ ሥነምግባር እንሰማለን።

አህመድ ት/ቤት ሲደርስ ሁልጊዜ በመጀመሪያ እበሩ ላይ የሚጠብቁትን የትምህርት ቤት የጥበቃ ሠራተኛ እንደምን አደሩ አባባ ሙስጠፋ በማለት ሰላምታ ይሰጣል፡፡ እሳቸውም ደስ ብሎአቸው ደህና አንተስ እንደምን አደርክ በማለት ሰላምታ ይሰጡታል፡፡ የት/ቤቱ የጽዳት ሠራተኛ የሆኑትን ወ/ሮ ዘምዘምንም እንዲሁ እንደምን አደሩ በማለት ሰላምታ ይሰጣል፡፡ አህመድ በት/ቤት ውስጥ የሚሠሩ ርዕሰ መምህር፣ ጸሀፊ፣ ነርስ፣ የሻይ ቤት ሠራተኞች እና መምህራን በስም ሁሉንም ያውቃቸዋል፡፡ ያከብራቸዋል፡፡ ከክፍል ጓደኞቹ ጋርም በፍጹም ተጣልቶ አያወቅም። አህመድ በት/ቤት ውስጥ ጥሩ ሥነ ምግባር ስላለው የትምህርት ቤቱ ሠራተኞችና አስተማሪዎች በጣም ይወዱት ነበር፡፡

**ጥያቄዎች**

1. አህመድ ት/ቤት ሲደርስ ሁልጊዜ ምን ያደርጋል?ለምን?
2. አህመድ የሚማርበት ት/ቤት የጽዳት ሠራተኛ ማን ይባላሉ?
3. አህመድ በት/ቤት ውስጥ የሚያውቃቸው እነማንን ነው?
4. አህመድ በት/ቤት ውስጥ ከጋደኞቹ ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት ነው?
5. የት/ቤቱ ሠራተኞችና አስተማሪዎች አህመድን ለምን ይወዱታል?

**ምክር፡**

አያችሁ ልጆች ጥሩ ሥነምግባር ካላችሁ ሁሉም ሰው ይወዳችኋል።

## 4ኛ ሳምንት

## «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሦስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን ነበር? እስቲ አስታውሶ የሚነገረን ማን ነው? አዎ! የሰማነው ተረት ስለ አህመድ ጥሩ ሥነምግባር ነበር። ዛሬ ደግሞ ስለ አህመድ የት/ቤት ባህርይ እንሰማለን።

አህመድ መምህርት ራህማ ሁልጊዜ የምትናገራቸውን የት/ቤት ህጎች ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ሁልጊዜ ያስታውሳል። ያከብራል፡፡ የት/ቤት ሥነሥርዓቶች ማለትም አያረፍድም፣ የክፍልና የቤት ሥራውን ሁል ግዜ በደንብ ይሰራል ንጽህናውን ይጠብቃል የራሱ ያልሆነን ነገር ሳያስፈቅድ አይነካም፣ ከክፍል ጓደኞቹ ጋር በመሆን ት/ቤቱን ያጸዳል ፡፡ አንድ ቀን ወድቆ ያገኘውን እርሳስ ፣መጽሐፍ፣ ገንዘብ እና ሰዓት ለት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ሰጥቷል። በት/ቤት ግቢ ወድቀው ያገኛቸውን ለት/ቤቱ በመስጠቱ እንዲሁም ሁሉንም መምህራን በማክበሩ አህመድ በት/ቤቱ ተሸላሚ ሆኗል፡፡

**ጥያቄዎች**

1. አህመድ ስለ ት/ቤት ህጎች ምን ያህል ያውቃል?
2. አህመድ በተለይ የሚያስታውሳቸው የት/ቤት ህጎች የትኞቹ ናቸው ?
3. ልጆች የራሳችሁ ያልሆነን ነገር ሳታስፈቅዱ መንካት ይቻላል? ለምን?
4. አህመድ በምን ምክንያት ተሸላሚ ሆነ?
5. በት/ቤት ግቢ ወድቆ የተገኘ የራስ ያልሆነ ንብረት ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

**ምክር፡**

አያችሁ ልጆች የት/ቤት ሥነሥርዓት ስናከብር ሁሉም ሠራተኞችና አስተማሪዎች እኛንም ይወዱናል እሺ!

## 4ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአራተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን ነበር? እስቲ አስታውሶ የሚነገረን ማን ነው? አዎ! የሰማነው ተረት ስለ አህመድ የት/ቤት ሥነሥርዓት ማክበር ነበር ።ዛሬ ደግሞ ስለ አህመድ የቅርብ ጓደኞች እንሰማለን፡፡

አህመድ በሚማርበት ክፍል ሦስት የቅርብ ጓደኞች ነበሩት፡፡ እነርሱም ገመቹ፣ አብዲና አልማዝ ናቸው፡፡ አህመድ፣ ገመቹ፣ አብዲና አልማዝ በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ አህመድ አብረውት በክፍል ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች ሁሉንም በስማቸው ያውቃቸዋል፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ አብሯቸው የሚጫወተውና የሚያጠናው ከገመቹ ከአብዲና ከአልማዝ ጋር ነው፡፡ እነሱ ለአህመድ የቅርብ ጓደኞቹ በመሆናቸው ከነሱ ጋር መጫወት ያስደስተው ነበር፡፡ ሲጫወቱም በፍጹም መዋደድ መተሳሰብና መከባበር ነበር። አህመድ በተለይ የፊደላትን ንባብና ቁጥር መቁጠርን ሲለማመድ እንዲሁም የቡድን ጨዋታ ሲጫወት ሁልጊዜ ከገመቹ ከአብዲና ከአልማዝ ጋር በመሆን ነበር፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የአህመድ የቅርብ ጓደኞች እነማን ናቸው? የእናንተስ የቅርብ ጓደኞች እነማን ናቸው?
2. አህመድ ከቅርብ ጓደኞቹ ጋር በመሆን ምን ያደርጋል? እናንተስ ምን ታደርጋላችሁ?
3. አህመድን ምን ያስደስተዋል? ለምን?
4. አህመድ በተለይ የፊደላትን ንባብና ቁጥር መቁጠርን ሲለማመድ ከማን ጋር መሆን ይፈልጋል? ለምን?

**ምክር፡**

አያችሁ ልጆች እናንተም የቅርብ ጓደኞች ሊኖሯችሁ ይገባል። ከነሱ ጋር ስታጠኑ እና ስትጫወቱ መዋደድና መከባበር ያስፈልጋችኋል።

## 4ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአምስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን ነበር? እስቲ አስታውሶ የሚነግረን ማን ነው? አዎ! የሰማነው ተረት ስለ አህመድ የቅርብ ጓደኞች ነበር ።ዛሬ ደግሞ ስለ አህመድና የክፍሉ ተማሪዎች ተግባራት እንሰማለን፡፡

አህመድ በሚማርበት ክፍል ሦስት የቅርብ ጓደኞች ነበሩት፡፡ አህመድና ጓደኞቹ በቡድን ስለሚያጠኑ ጎበዝ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ አንድ ቀን በቡድናቸው ተሰባስበው በቀን ውስጥ ምን መሥራት እንዳለባቸው ተወያዩ፡፡ መጀመሪያ አልማዝ ጠዋት ተነስተን በቶሎ ት/ቤት መምጣት አለብን አለች፡፡ ገመቹም በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የአስተማሪያችን ትዕዛዛት ማክበር አለብን አለ። አብዲም ገመቹ አሁን ያልከውን ነገር ብታብራራልን ደስ ይለኛል አለ። ገመቹም እንዲህ ሲል አብራራ ለምሳሌ መምህርቷ ተረት ስትነግረን በደንብ እናዳምጥ። የምትጠይቀንን ጥያቄዎች እጃችንን አውጥተን እንመልስ። የምትሰጠንን የልምምድ ሥራ በደስታ እንስራ። የቡድን ጨዋታ ላይ ህጎቹን ጠብቀን እንጫወት። መዝሙሮቻችንንም ጮክ ብለን እንዘምር። ትምህርታችንን ከጨረስን በኋላ ቀን ላይ እንጫወት፡፡ ከዚያም ከሰዓት በኋላ ወደ ቤታችን ሄደን ትንሽ ተጫውተን እናጥና፡፡ ሲመሽና ማታም እራታችን በልተን ቶሎ ብለን እንተኛ ብሎ በዝርዝር አብራራ፡፡ አህመድ ውይይቱ ላይ ሁሉንም አመስግኖ እኔ የምጨምረው ነገር የለኝም አሁን የተወያየንበት ነገር ጥሩ ስለሆነ በተግባር ማዋል አለብን አለ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ በቡድናቸው ውስጥ ሁልጊዜም እንደተባባሉት ያደርጉ ነበር፡፡

**ጥያቄዎች**

1. አህመድና ጋደኞቹ በቀን ውስጥ ምን ምን ይሰራሉ?
2. የሚያከናወኑትን ተግባራት ተናገሩ። ጠዋት ላይ? በክፍል ውስጥ? ከክፍል ውጭ?
3. አስተማሪያቸው የምትሰጣቸው ትዕዛዛት ምን ምን ናቸው?
4. አህመድና ጓደኞቹ ለምን ጎበዞች ተባሉ?

**ምክር፡**
ልጆች እናንተም ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን በቀን ውስጥ ስለምታደርጉት ነገር መወያየት አለባችሁ፡፡ ሁልጊዜም የተባባላችሁትን ማድረግ አለባችሁ፡፡

# 5ኛ ሳምንት

## "ከዕለታት አንድ ቀን"

## 5ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአንደኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ሳምንት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች፤ ልክ ናችሁ። ባለፈው ሳምንት ስለ አህመድ መልካም ሥነምግባር ነበር። ዛሬ ደግሞ ስለ ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው በሰላምና በደስታ መኖር እንሰማለን።

ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው በአንድ ኢንዚ በተባለች መንደር ውስጥ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው ጠዋት ሲነሱም ሆነ ማታ ከሥራቸው ሲገቡ ይገናኛሉ፡፡ የወ/ሮ ዘሃራ ጎረቤቶች በቁጥር 5 ይሆናሉ፡፡ ሲገናኙም እንደምን አደራችሁ? እንደምን ዋላችሁ? ይባባላሉ፡፡ አብረው በመኖራቸው ደስ ይላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በእረፍት ቀን ወ/ሮ ዘሃራ ሻይ አፍልተው ጎረቤቶቻቸውን ይጠራሉ፡፡ ከዚያም አምስቱም አብረው ሻያቸውን እየጠጡ ስለ ሥራቸው፣ ስለ ልጆቻቸው፣ ስለጤናቸው ይነጋገራሉ፡፡ በሌላ ቀን ደግሞ ወ/ሮ ፋጡማ ቡና አፍልተው አምስቱንም ጎረቤቶች ይጠሩዋቸውና እንደዚሁ አብረው ይጫወታሉ፣ የታመመ ሰው ካለም በሕብረት ሄደው የጠይቃሉ፣ የሚያስፈልጉ ነገሮችንም ይወስዱላቸዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው በሰላምና በደስታ ለረዥም ጊዜ አብረው ኖረዋል፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የእነ ወ/ሮ ዘሃራ መንደር ማን ትባላለች?
2. ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው ምን ጊዜ ይገናኛሉ?
3. የእነ ወ/ሮ ዘሃራ ጎረቤቶች ስንት ናቸው?
4. ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው በእረፍት ቀናት ምን ይሰራሉ?
5. እነ ወ/ሮ ዘሃራ ለምን ደስተኞች የሆኑ ይመስላችኋል?

**ምክር፡**

አያችሁ ልጆች እናንተም ለጎረቤቶቻችሁ እና ለጓደኞቻችሁ መልካም በመሆን ከነሱ ጋር በሰላምና በደስታ መኖር አለባችሁ።

## 5ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሁለተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን እንደነበር የሚያስታውስ አለ? አዎ! ልክ ነው። ስለ ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው በሰላምና በደስታ መኖር ነበር። ልጆች ዛሬ ደግሞ ስለ መጓጓዣ ዓይነቶች እንሰማለን።

ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው አንዳንድ ጊዜ ከከተማ ውጭ ሄደው ይዝናኑ ነበር፡፡ ለዚህም የሚጠቀሙት የጎረቤታቸውን የአቶ ከድርን መኪና ነበር፡፡ አቶ ከድር በሽርሽር ወቅት መኪናቸውን ነጃጅ ሞልተውና ጎማዋን ቀይረው አምስቱንም ጎረቤቶቻቸውንና አራቱን ልጆች በአንድ ላይ ዘጠኝ ሆነው ይሄዱ ነበር፡፡ እዚያም ቀኑን ሙሉ ከተዝናኑ በኋላ ማታ ተመልሰው ሁሉም ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸውም አቶ ከድርን በጣም ያመሰግኗቸው ነበር፡፡ ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው መኪናን ሲጠቀሙ በመንደሩ ያሉ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ፈረስ፣ አህያና በቅሎን በመጓጓዣነት ይጠቀማሉ፡፡ ዕቃዎችን ለማጓጓዝም አህያ የሚጎትተወን ጋሪ ይጠቀማሉ፡፡ የነወ/ሮ ዘሃራ መንደር ሰዎች ሥራዎቻቸው እንዲቀልላጠፉላቸው የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ይጠቀሙ ነበር፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው አንዳንድ ጊዜ ከከተማ ውጭ የሚሄዱት ለምን ነበር?
2. ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው ከከተማ ውጭ በምን ይሄዱ ነበር?
3. ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው ከተማ ውጭ ሲሄዱ ስንት ሆነው ነው?
4. በነወ/ሮ ዘሃራ መንደር ያሉ ሰዎች ለመጓጓዣነት የሚጠቀሙት በምንድን ነው?
5. በነወ/ሮ ዘሃራ መንደር ያሉ ሰዎች አህያ የሚጎትተወን ጋሪ ለምን ይጠቀማሉ?

**ምክር፡**

ልጆች በእናንተስ አካባቢ የምትጠቀሙባቸው የመጓጓዣ ዓይነቶች ምን እና ምን ናቸው፡፡ ወደየትስ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? አያችሁ ልጆች የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች ስላሉ እንደአካባቢው ሁኔታ መጠቀም ይቻላል።

## 5ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሦስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን ነበር? እስቲ አስታውሶ የሚነገረን ማን ነው? አዎ! የሰማነው ተረት ስለ መጓጓዣ ዓይነቶች ነበር። ዛሬ ደግሞ በእነ ወ/ሮ ዘሃራ መንደር ስለሚገኙ አስፈላጊ ተቋማት እንሰማለን።

ወ/ሮ ዘሃራ እና ቤተሰቦቻቸው በትንሿ መንደራቸው ከጎረቤቶቻቸው ጋር በሰላምና በደስታ ሲኖሩ የተወለዱት ልጆች አደጉ፡፡ እነሱም አብዲ፣ ሙስጠፋ፣ ሮዛ እና ሃዊ ናቸው፡፡ እነዚህን ሕፃናት ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው ወደ ት/ቤት ወሰዱና አስገቧቸው፡፡ በት/ቤት ሲማሩም አልፎ አልፎ በጤና ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ሐኪሞች እየመጡ ክትባት ይከትቧቸው ነበር፡፡ በመሆኑም የሕፃናቱ ጤና ተጠብቆ ትምህርታቸውን ይማራሉ፡፡ ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው በአቅራቢያቸው የሚገኘውን ባንክ ቤትም በመጠቀም ብራቸውን ይቆጥቡ ነበር፡፡ በወር አንድ ጊዜ ደግሞ ከባንክ ቤት ብር አውጥተው ወደ ወፍጮ ቤት በመሄድ የሚያስፈልጋቸውን ያህል እህል ያስፈጫሉ፡፡ ወደ ገበያ በመሄድም አስፈላጊ የምግብ ዓይነቶችን በመግዛት ቤተሰቦቻቸውን ይመግቡ ነበር፡፡ በነወ/ሮ ዘሃራ መንደር የሚያስፈልጉ ተቋማት ስለሚገኙ ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው ሳይቸገሩ በደስታ ይኖሩ ነበር፡፡

#### ጥያቄዎች

1. ወ/ሮ ዘሃራ እና ቤተሰቦቻቸው በትንሿ መንደራቸው ከጎረቤቶቻቸው ጋር በሰላምና በደስታ ሲኖሩ የተወለዱት ልጆች እነማን ይባላሉ?
2. ለሕጻናቱ ክትባት የሚሰጡት ምን የሚሰሩ ሰዎች ናቸው? ክትባቱንስ የሚከትቡት የት ነው?
3. ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው በአቅራቢያቸው የሚገኘውን ባንክ ምን ያደርጋሉ? ለምን?
4. ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው ወፍጮ ቤት የሚሄዱት ለምንድን ነው? ገበያስ?
5. ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው ሳይቸገሩ በደስታ የኖሩት ለምን ይመስላችኋል?

**ምክር፡**

**አያችሁ ልጆች በአንድ መንደር ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት አሉ። በነኝህ ተቋማት በአግባቡ መገልገል ይኖርብናል እሺ!**

## 5ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአራተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን ነበር? እስቲ አስታውሶ የሚነግረን ማን ነው? አዎ! የሰማነው በእነ ወ/ሮ ዘሃራ መንደር ስለሚገኙ አስፈላጊ ተቋማት ነበር ። ዛሬ ደግሞ መንደራቸው ለመኖርያ ተስማሚ ስለመሆኑ እንሰማለን፡፡

*ወ/ሮ ዘሃራ ሁልጊዜ ሐሙስ በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው ገበያ በመሄድ የእንስሳትና የዕጽዋት ተዋጽዖዎችን ይገዛሉ፡፡ ይኸውም ከዕጽዋት ዓይነቶች፣ ፍራፍሬና የጓሮ አትክልት እንዲሁም ጤፍ እና ሩዝ ይገዛሉ፡፡ ከእንስሳት ተዋጽዖዎች ደግሞ እንቁላል፣ ሥጋ እና ወተት ይገዛሉ፡፡ ወ/ሮ ዘሃራ በተቻላቸው መጠን ቤተሰቦቻቸውን ሁልጊዜ የተመጣጠነ ምግብ ይመግባሉ፡፡ በተጨማሪም እነወ/ሮ ዘሃራ ሰፈር የቧንቧ ውሃ አለ፡፡ ይህ የቧንቧ ውሃ የሚመጣው በመንደራቸው ከሚገኘው ወንዝ ሲሆን የተጣራ ውሃ በቧንቧ አልፎ በነወ/ሮ ዘሃራ ግቢ እና በጎረቤቶቻቸውም ግቢ ውስጥ ንጹህ ውሃ እንደልብ ያገኛሉ፡፡ በመሆኑም እነወ/ሮ ዘሃራ የሚመገቡትን ምግብና የሚጠጡትን ውሃ በአቅራቢያቸው በቀላሉ ያገኛሉ፡፡ የእነወ/ሮ ዘሃራ መንደር ለመኖርያ በጣም ተስማሚ በመሆኑ የመንደሩ ሰዎች በዚህ ደስተኞች ሆነው ይኖሩ ነበር፡፡*

**<u>ጥያቄዎች</u>**

1. ወ/ሮ ዘሃራ በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው ገበያ የሚሄዱት ምን ቀን ነው? ምን ለመግዛት ነው?
2. ወ/ሮ ዘሃራ ከዕጽዋት ዓይነቶች ምን ምን ይገዛሉ ? ከእንስሳት ተዋጽዖዎችስ?
3. እነወ/ሮ ዘሃራ የሚጠጡትን ውሃ ከየት ያገኛሉ ? ውሃው ለምን ንጹህ የሆነ ይመስላችኋል?
4. ወ/ሮ ዘሃራ በተቻላቸው መጠን ቤተሰቦቻቸውን ሁልጊዜ የተመጣጠነ ምግብ ለምን የሚመግቡ ይመስላችኋል?
5. የእነወ/ሮ ዘሃራ መንደር ሰዎች ለምን ደስተኞች የሆኑ ይመስላችኋል?

**ምክር፡**

አያችሁ ልጆች የነወ/ሮ ዘሃራ መንደር ለመኖርያ በጣም ተስማሚ ነው፡፡ የእናንተስ?

## 5ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአምስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን ነበር? እስቲ አስታውሶ የሚነገረን ማን ነው? አዎ! የሰማነው ተረት የእነወ/ሮ ዘሃራ መንደር ለመኖርያ ተስማሚ ስለመሆኑ ነበር። ዛሬ ደግሞ ስለ አካባቢ ጽዳት እንሰማለን፡፡

ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው በሣምንት አንድ ቀን የአካባቢ ጽዳት ያከናውናሉ፡፡ ይህንንም ተግባር በህብረትና በመመካከር ያደርጉታል፡፡ በመንደራቸው የጽዳት ቀን አምስቱ ጎረቤቶቻቸውና አራት ልጆቻቸው በጠዋት ተነስተው መጥረጊያ፣ የቆሻሻ መሰብሰቢያና ማጠራቀሚያ ይዘው ከግቢዎቻቸው በመጀመር መንገዱን ሁሉ ያፀዳሉ፡፡ የውሃ መውረጃ ቦዮች እንዳይደፈኑ በጥንቃቄ ቆሻሻዎችን ያነሳሉ። ስለሆነም የእነ ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው ልጆች ከጽዳት ጉድለት በሚመጣ በሽታ ተጠቅተው አያውቁም፡፡ ልጆቹም አካባቢያቸውን በንጽህና በመጠበቅ ራሳቸውን ከበሽታ እንደሚከላከሉ በት/ቤት የተማሩትን ተግባራዊ በማድረጋቸው ዘወትር ደስተኞች ሆነው ይኖሩ ነበር፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው የአካባቢ ጽዳት የሚያከናውኑት መቼ ነው?
2. ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው ለመንደራቸው ጽዳት ምን ዓይነት ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ?
3. የውሃ መውረጃ ቦዮች ቢደፈኑ በመንደሩ ምን ሊከሰት ይችላል?
4. ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው መንደራቸውን በማጽዳታቸው ምን ዓይነት ጥቅም ያገኛሉ?
5. የእነ ወ/ሮ ዘሃራ እና ጎረቤቶቻቸው ልጆች ዘወትር ደስተኞች ሆነው የኖሩት ለምን ይመስላችኋል?

**ምክር፡** አያችሁ ልጆች አካባቢያችንን በንጽህና በመጠበቅ ራሳችን ከበሽታ እንከላከላለን፡፡

# 6ኛ ሳምንት

## "ከዕለታት አንድ ቀን"

# 6ኛ ሳምንት

## «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአንደኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ሳምንት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች\ ልክ ናችሁ። ባለፈው ሳምንት ስለ ወ/ሮ ዘሃራና ጎረቤቶቻቸው በሰላምና በደስታ መኖር እንዲሁም ስለመንደራቸው ለኑሮ አመቺነት ነበር የሰማነው። ዛሬ ደግሞ አብዲና ጓደኞቹ ስላደረጉት ትምህርታዊ ጉብኝት እንሰማለን።

አንድ ቀን የነአብዲ መምህር ነገ ለትምህርታዊ ጉብኝት በት/ቤታችን አካባቢ ወደ ሚገኘው የመናፈሻ ቦታ እንሄዳለን አለቻቸው፡፡ መምህራቸው ያለችውን ሲሰሙ አብዲና ጓደኞቹ በጣም ተደሰቱ፡፡ በጉብኝቱም ቀን በጥዋት ተነሥተው አብዲና ጓደኞቹ ወደ ት/ቤት ሄዱ፡፡ ከዚያም ከመምህራቸው ጋር በመሆን ወደ አንድ መናፈሻ ሥፍራ ሄዱ። እንደደረሱም ብዙ ደስ የሚሉ ለዓይን የሚማርኩ ተክሎችን አዕዋፍን የድንጋይ ዓይነቶችን፣ የአፈር ዓይነቶችን፣ ጠጠሮችን፣ አሸዋ ተመለከቱ፡፡ በተመለከቷቸው ነገሮች በጣም ተደሰቱ፡፡ አብዲና ጓደኛቹ "እነዚህ የምናያቸው ነገሮች ሁሉ ምን ይባላሉ?" ብለው መምህራቸውን ጠየቋት፡፡ መምህርም "እነዚህ የምታዩዋቸው ነገሮች ሕይወት ያላቸውና፣ ሕይወት የሌላቸው በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ሕይወት ያላቸው የሚባሉት እንደ እንስሳት፣ ተክሎች፣ አዕዋፍ፣ ሲሆኑ ሕይወት የሌላቸው የሚባሉት ደግሞ እንደ ድንጋይ፣ ውሃ፣ አሸዋ፣ አፈር፣ ፀሐይ ያሉት ናቸው" አለቻቸው፡፡ መምህራቸውም "ሕይወት ያላቸውም ሕይወት የሌላቸውም ነገሮች ለሰው ልጅ አስፈላጊና ጠቃሚ ናቸውና አካባቢያችንን ልንንከባከብ ይገባናል፡፡" አለቻቸው፡፡

አብዲም "በኋላ እንድንጫወትበት እነዚህን ፍሬዎች፣ ጠጠሮች እና አበቦች እኔና ጓደኞቹ ለቅመን መውሰድ እንችላለን?" ብሎ መምህሩን ፈቃድ ጠየቀ፡፡ መምህሯም "ፍሬና ጠጠሮችን ለቅማችሁ ውሰዱ አበቦቹን ግን መቁረጥ አይፈቀድም፤ ተክሎችን መንከባከብ ያስፈልጋል እንጂ መቁረጥ የለባችሁም።" አለቻቸው፡፡ ከዚያም አብዲና ጓደኞቹ አስር ፍሬዎች እና አስር ጠጠሮች ለቅመው ያዙ፡፡ ከዚያም ጉብኝታቸውን ጨርሰው ወደ ት/ቤታቸው ተመለሱ ይባላል፡፡

***<u>ጥያቄዎች</u>***

1. አብዲና ጓደኞቹ ከመምህራቸው ጋር ጉብኝት ሄደው ምን አዩ?
2. ህይወት ያላቸው ነገሮች እነማን ናቸው? ሕይወት የሌላቸውስ?
3. ተክሎችን ለምን መንከባከብ ያስፈልገናል?
4. አብዲና ጓደኞቹ ከጉብኝቱ ቦታ ምንይዘው ወደ ት/ቤታቸው ተመለሱ? ለምን?
5. ህይወት ያላቸው ነገሮች የሰው ልጅን እንዴት የሚጠቀሙ ይመስላችኋል?
6. ህይወት የሌላቸው ነገሮችን ለምን ልንጠቀምባቸው እንችላለን?

***<u>ምክር</u>***፡-ሊያችሁ ልጆች በአካባቢያችሁ የምታገኟቸውን ሕይወት ያላቸውም ሆኑ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ለሰው ልጅ አስፈላጊና ጠቃሚ ስለሆኑ ልትንከባከቧቸው ይገባል፡፡

## 6ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሁለተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት አብዲና ጓደኞቹ ከመምህራቸው ጋር በመሆን ጉብኝት ሄደው ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ጎብኝተው እንደተዋወቋቸው ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለ አብዲና ጓደኞቹ የቤት እንስሳት ትውውቅ እንሰማለን፡፡

የአብዲ ቤተሰቦች አንድ ውሻ፣ ሁለት አህዮች፣ ሦስት ፈረሶች፣ አንድ ድመትና አራት ላሞች ነበሯቸው፡፡ የአብዲ ጓደኞች ኢብራሂምና አሊ የቤት እንስሳቱን ለማየት አዘውትረው እነ አብዲ ቤት በመሄድ እንስሳቶቹን እያዩ ይደሰቱ ነበር፡፡ እንዲሁም ከአብዲ ጋር በመሆን ለእንስሳቶቹ ምግብ ይሰጧቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን እንደ ሁልግዜ ሁሉ ኢብራሂም እና አሊ ወደ እነ አብዲ ቤት ሄደው ከአብዲ ጋር ላሞቹን፣ አህዮቹንና ፈረሶቹን ሣር እንዲግጡ ወደ ሜዳ ወሰዷቸው፡፡ ወደ ሜዳውም እንደ ደረሱ እንስሳቶቹ ሣር እንዲግጡ ወደ ሜዳ ለቀቋቸውና ሦስቱ ጓደኛሞች አባሮሽ መጫወት ጀመሩ፡፡ እነሱ ጨዋታቸውን ሲጫወቱ አንዷ ፈረስ ከሌሎቹ እንስሶች ተለይታ ወደ ሌላ ቦታ ሄዳለች፡፡ በኋላ እነ አብዲ ጨዋታቸውን ጨርሰው ወደ ቤት ለመመለስ አህዮቹንና ፈረሶቹን ከየአሉበት ቦታ ሲሰበስቡ አንዷ ፈረስ የለችም፡፡ ጠፍታ ሄዳለች፡፡ በጣም ደነገጡ፣ ወደዚያ ወደዚህ ቢሯሯጡ አላገኟትም፡፡ እጅግ አዘኑ፡፡ ቁጭ ብለው ሲያለቅሱ ከሩቅ አንድ ሰው ፈረስ እየነዳ ሲመጣ አዩ፡፡ "ያ ሰውዬ እየነዳ የሚያመጣት ፈረስ የማንናት? የጠፋችው የኛ ፈረስ ትሆን?" እያሉ ሲጨነቁ ሰውየው ወደ እነሱ እየቀረበ ሲመጡ ለካ የአብዲ አባት አቶ መሐመድ ናቸው፡፡ አቶ መሐመድ ከገበያ ሲመለሱ ፈረሷ ዝም ብላ መንገድ ተከትላ ስትሄድ እንዳገኟትና የሳቸው ፈረስ እንደሆነች ስለአወቁ ይዘዋት እንደተመለሱ ለአብዲና ለጓደኞቹ ነገሯቸው፡፡ አቶ መሐመድም እናንተ እንስሳቱን ልትመግቧቸው ይዛችሁ ከወጣችሁ በደንብ መጠበቅና እንዲመገቡ በማድረግ ወደ በረታቸው መመለስ አለባችሁ እንጂ እነሱን የትም ጥላችሁ በጫዋታ ብቻ ግዜያችሁን ማሳለፍ የለባችሁም ብለው ከተቆጧቸው በኋላ ሁሉም አንድ ላይ እንስሳቶቹን ይዘው ወደ ቤት ተመለሱ ይባላል፡፡

**ጥያቄዎች**

1. እነአብዲ ያሏቸው እንስሳቶች ምን ምን ናቸው?
2. እነ አብዲ እንስሳቶችን ወደ ሜዳ ለምን ወሰዷቸው?
3. አብዲና ጓደኞቹ ፈረሷ ስትጠፋባቸው ምን አደረጉ?
4. የጠፋችውን ፈረስ ማን አገኛት?
5. የአብዲ አባት እነ አብዲን ለምን ተቆጧቸው?

**ምክር**፡- ስለዚህ ልጆች በሥራ ሰዓት ሥራ፣ በጨዋታ ሰዓት ጨዋታ በማድረግ ኃላፊነታችሁን በአግባቡ መወጣት አለባችሁ፡፡ እሺ፡፡

# 6ኛ ሳምንት

## «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሦስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት አብዲና ጓደኞቹ ፈረስና አህዩችን ይዘው ሣር እንዲግጡ ወደ ሜዳ ይዘዋቸው እንደሄዱና ከእንስሳቶቹ መሆል አንድ ፈረስ ጠፍታ የአብዲ አባት አቶ መሐመድ እንዳገኟት ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ አብዲ ስለሚወዳቸው የቤት እንስሳት እንሰማለን።

አብዲ የቤት እንስሳትን በጣም ነው የሚወደው ከትምህርት ቤቱ ሲመለስ ከድመቶቹ፣ ከውሾቹ፣ ከአህዮቹ፣ ከበጎችና ፍየሎች ጋር መጫወት ደስ ይለዋል፡፡

አንድ ቀን፣ አሊና ኢብራሂም ከአብዲ ጋር እንጫወት ብለው ወደ እነአብዲ ቤት ሄዱ፡፡ የአብዲ እናት ወ/ሮ ፋጡማ የአብዲን ጓደኞች ልክ እንደ አብዲ ይወዷቸው ስለነበር የአብዲ ጓደኞች ሲመጡ በጣም ደስ አላቸው፡፡ ከዚያም ወ/ሮ ፋጡማ የአብዲን ጓደኞች በሉ ከአብዲ ጋር ሆናችሁ ዛሬ ለቤት እንስሳቱ ምግብ የምትሰጡት እናንተ ናችሁ ብለው ትዕዛዝ ሰጧቸው፡፡ ኢብራሂም "ድመቷንና ልጆቿን ወተት በጎድጓዳው ሣህን አድርገህ መግባቸው፡፡ ወተትም ሲያንስ ጨምርላቸው" አሉት፡፡ አሊን ደግሞ "ለአራቱ በጎችና ለአምስቱ ፍየሎች ከዚያ ከሣር ክምር ላይ አምጥተህ ሜዳው ላይ አድርገህ ስጣቸውና ይብሉ" አሉ፡፡ አብዲን ደግሞ "ለውሻው ከዚያ ከአጥሩ ላይ ከተንጠለጠለው አጥንት አንዱን አምጥተህ ስጠውና ይቆርጥም" አሉት፡፡ አብዲና ጓደኞቹ ሥራ በመታዘዛቸው ተደስተው በታዘዙት መሠረት ለእንስሳቶቹ ምግባቸውን እንዲመገቡ አደረጉ፡፡ ወ/ሮ ፋጡማም ሶስቱ ጓደኛሞች የታዘዙትን በአግባቡ ስለሠሩ አመሰገኗቸው ይባላል፡፡

**ጥያቄዎች**

1. አብዲ በጣም የሚወደው ምንን ነው?
2. የአብዲ እናት ስም ማን ይባላል?
3. ወ/ሮ ፋጡማ አብዲና ጓደኞቹን ምን አዘዟቸው?
4. ድመቷና ልጆቿን ምን መገቧቸው?
5. በጎቹና ፍየሎቹ እንዲመገቡ ምን ሰጧቸው?

**ምክር**፡- አያችሁ ልጆች አብዲና ጓደኞቹ የአብዲ እናት ያዘዟቸውን ሁሉ ሠሩ፡፡ ጥሩ ልጆች ናቸው፡፡ እናንተም እንደነሱ የቤት እንስሳትን ውደዱ፣ እማማና አባባ ሲያዟችሁ ደግሞ ሥሩ፡፡ እንስሳቶችን መንከባከብና መመገብ ውደዱ፡፡ እሺ ልጆች፡፡

## 6ኛ ሳምንት

## «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአራተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት አብዲና ጓደኞቹን ወ/ሮ ፋጡማ የአብዲ እናት አዘዋቸው የቤት እንስሳቱን እንዴት እንደመገቧቸው ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ የአብዲ እናት ለአብዲና ጓደኞቹ ስለዱር እንስሳት የነገሯቸውን ተረት እንሰማለን፡፡

የአብዲ እናት ተረቱን ሲጀምሩ "ተረት ተረት" ሲሉ። አብዲና ጓደኞቹም "የላም በረት" ብለው መለሱ። የአብዲ እናትም ቀጥለው "ከዕለታት አንድ ቀን የዱር እንስሳት ተሰብስበው የሩጫ ውድድር እናድርግ አሉ፡፡ አራዊቶቹ ሁሉ በጣም ተደሰቱ ሁሉም ለመሮጥ ዝግጅት አድርገው ወደ ሩጫ ሜዳው መጡ፡፡ ከዚያም ዳኞች ተሰበሰቡና መጀመሪያ ማንና ማን ይሩጡ ብለው ተወያዩ ከዚያም ጥንቸልና ኤሊ እንዲሮጡ ተስማሙ፡፡ በመሆኑም ጥንቸልና ኤሊ የሩጫ ቦታቸውን ይዘው ተዘጋጁ፡፡ ዳኞቹም ፊሽካ በመንፋት ሩጫው ተጀመረ፡፡ ጥንቸል በጣም በፈጣን ሁኔታ ሮጦ እንዳጋመሰ ጥንቸልን ሲያያት ገና ሩቅ ነበረች፡፡ እሷ እኔጋ እስክትደርስ ለምን ዛፍ ጥላ ሥር አረፍ አልልም በማለት አንድ ዛፍ ሥር ጋደም አለ፡፡ በዚያውም እንቅልፍ ይዞት ሄደ፡፡ ኤሊም ቀስ ብላ ደረሰችበት፡፡ ጥንቸል ግን በጣም ተኝቶ ስለነበር አልነቃም፡፡ ከዚያም ኤሊ የመጨረሻ መሥመሩን አልፋ ገባች። የዱር እንስሳትም በሙሉ አጨበጨቡ። በኤሊ ጉብዝናም በጣም ተደነቁ፡፡ ጥንቸልም ጫጫታው ምንድነው ብሎ ሲነቃ ኤሊ አሸንፋ መሆኑ ገባው፡፡ ከዚያም በመተኛቱ ተፀፀተ፡፡ አይገርምም!

ተረቴን መልሱ መልሱ መልሱ  
አፌን በዳቦ አብሱ አብሱ።" በማለት ተረታቸውን ጨረሱ።

<u>**ጥያቄዎች**</u>

1. የዱር አራዊቶች ተሰብስበው ምን አሉ?
2. በመጀመሪያ ለሩጫ ውድድር የተመረጡት እነማን ነበሩ?
3. ከዚያ በኋላ ኤሊ እንዴት ሊያሸንፍ ቻለ?
4. ጥንቸል በመተኛቱ ምን ተሰማው?
5. የዱር አራዊቶች በኤሊ ማሸነፍ ምን አሉ?

**<u>ምክር</u>**፡- እናንተም ልጆች ጉረኛ መሆን የለባችሁም፡፡ ጥንቸል በጣም ጉረኛ ስለነበር በኤሊ ተሸነፈ፡፡ ስለዚህ ከጓደኞቻችሁ ጋር ስትጫወቱ ተቀባይነት ያላቸውን ባህርያት ማሣየት አለባችሁ፡፡

## 6ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአምስተኛው ቀን)

ባለፈው ዕለት የአብዲ እናት ለአብዲና ጓደኞቹ ስለ ዱር እንስሳት የነገሯቸውን ተረት ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ የቤት እንስሳት የልጆቻቸው ስም ምን እንደሚባል እንሰማለን፡፡

አንድ ቀን መምህራቸው አብዲን እንዲህ ስትል ጠየቀችው፡፡ እናንተ ቤት ምን ምን የቤት እንስሳት አሉ? ብላ ጠየቀችው፡፡ አብዲም እኛ ቤት ድመት፣ ውሻ፣ አህያ፣ ፈረስ፣ ላም፣ በሬ አሉን አላት፡፡ ብዛታቸውስ ምን ያህል ነው አለችው፡፡ አንድ ድመት፣ እና ሁለት ለጆቿ፡፡ አራት አህዮች፣ አምስት ላሞች፣ ሁለት በሬዎች አሉን አላት፡፡ ጎበዝ አብዲ ቁጥራቸውንም በደንብ ታውቃለህ አለች፡፡ እንደዚህ ስታደንቀው አብዲም ደስ አለው፡፡ መምህሯም እንስሳትን የሚያሳይ ሥዕል ዘርግታ እያሳየቻቸው "እስኪ ልጆች ይህንን ሥዕል ተመልከቱና ከነኝህ ውስጥ የቤት እንስሳት የሆኑትን ንገሩኝ" አለቻቸው። ሕፃናቱ ሥዕሉን ሲያዩ በጣም ተደሰቱ። አሁን አጠገባቸው ያሉ መሰላቸው፡፡ በየተራ እየተነሱ ዳሰሷቸውና የቤት እንስሳት የሆኑትን እየጠቀሙ ስማቸውን ነገሯት፡፡ በሥዕሉ ላይ የሚታዩትን የቤት እንስሳ ሥዕልም ቆጥረው ብዛቱን ተናገሩ፡፡ መምህሯም ልጆች ጎበዝ ሆነው የቤት እንስሳትን አውቀው ስማቸውን ስለነገሯት በጣም ደስ አላት፡፡ ከተማሪዎቹ መካከል የነአብዲ ጓደኛ የሆነችው ዘሃራ መምህሯን አንድ ጥያቄ ጠየቀች። የእነዚህ የቤት እንስሳት ልጆች ምን ይባላሉ? ብላ ጠየቀች፡፡ መምህሯም "ጎበዝ ዘሃራ! ጥሩ ጥያቄ ነው።" አለችና የቤት እንስሳቱን ልጆች ስም እንዲህ እያለች መናገር ጀመረች

- የድመት ልጅ ሙጭሊት ትባላለች፣
- የውሻ ልጅ ቡችላ ትባላለች፣
- የአህያ ልጅ ውርንጭላ ትባላለች፣
- የበግ ልጅ ግልገል ትባላለች፣
- የላም ልጅ ጥጃ ትባላለች ብላ ነገረቻቸው፡፡

"ስለዚህ ልጆች የቤት እንስሶች ብዙ ጥቅም ስላላቸው በደንብ ተንከባክበን እንያዛቸው" አለቻቸው ይባላል፡፡

<u>**ጥያቄዎች**</u>

1. መምህራቸው አብዲን ምን ብላ ጠየቀችው?
2. እነ አብዲ ቤት ስንት የቤት እንስሳት አሉ?
3. መምህራቸው ሥዕሉን ዘርግታ ምን አሳየቻቸው?
4. የነ አብዲ ጓደኛ መምህሯን ምን ብሎ ጠየቃት?
5. የቤት እንስሳን ልጆች ስም መምህሯ ምን ምን ይባላሉ አለች?

<u>**ምክር**</u>፡- ልጆች የቤትእንስሳት ለምግብነት ለሥራ ለጥበቃ ስለሚያገለግሉ ሳንመታቸው ምግባቸውንም በመስጠት በእንክብካቤ ልንይዛቸው ይገባል እሺ ልጆች፡፡

# 7ኛ ሳምንት

## "ከዕለታት አንድ ቀን"

## 7ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአንደኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ሳምንት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች! ልክ ናችሁ። ባለፈው ሳምንት አብዲና ጓደኞቹ ስላደረጉት ትምህርታዊ ጉብኝት እንዲሁም ሰለሚያውቋቸው የቤት እና የዱር እንስሳት ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ከድጃና ጓደኞቿ በአካባቢያቸው የሚገኙትን ዛፎች እንዴት እንደሚንከባከቧቸው እንሰማለን፡፡

ከድጃ የምትባል የአፀደ ሕፃናት ተማሪ ነበረች፡፡ ከድጃ በአካባቢዋ አብረዋት የሚጫወቱና የሚያጠኑ ሁለት ጓደኞች ነበሯት፡፡ ስማቸውም ነኢማና ሳድያ ይባላሉ፡፡ ሦስቱም ጓደኛሞች በጣም ይዋደዳሉ፡፡ አንድ ቀን እነዚህ ሦስት ጓደኛሞች ከነከድጃ ቤት ጀርባ ባለው ሜዳ ለመጫወት ተያይዘው በቤቱ ጀርባ ሲሄዱ ነኢማና ሳዲያ ትላልቅ የሚያማምሩ ሦስት ዛፎች አዩ፡፡ እቤት እነዚህ ዛፎች ሲያምሩ! ማነው የተከላቸው ብለው ከድጃን ጠየቋት፡፡ ከድጃም አባቴ ነው የተከላቸው አለቻቸው፡፡ እነሱም በጣም ደስ ይላሉ አሏት፡፡ ስማቸው ማን ይባላል አሏት፡፡ ከድጃም እኔ ስማቸውን አላውቅም እስኪ አባቴ ጋ እንሂድና እንጠይቀው እሱ ይነግረናል አለቻቸው፡፡ ጓደኞቿም እሺ ደስ ይለናል አሉና ተያይዘው አባቷ ወደ አለበት ቦታ ሄዱ፡፡ የከድጃ አባት አቶ መሐመድም የከድጃን ጓደኞችና ከድጃን ሲያዩ በጣም ደስ አላቸው፡፡ ከዚያም ከድጃ፤ አባዬ እኔና ጓደኞቼ እኛ ቤት ጓሮ ተተክለው ያሉትን የሦስቱን ዛፎች ስም ልንጠይቅህ ነው የመጣነው ስትል ጠየቀች፡፡ አቶ መሐመድም እሺ ብለው ዛፎቹ ወደሚገኙበት ቦታ ከልጆቹ ጋር አብረው ሄዱ፡፡ ከዚያም በየተራ የዛፎቹን ስም እንዲህ በማለት ነገሯቸው፡፡ ይሄ መጀመሪያ ላይ የሚገኘው ረዥሙ የባህር ዛፍ ይባላል፣ ቀጥሎ የሚገኘው ደግሞ የጥድ ዛፍ ይባላል፣ በመጨረሻ የሚገኘው ደግሞ የወይራ ዛፍ ይባላል በማለት ዛፎቹን አስተዋወቋቸው፡፡ የከድጃ ጓደኞችም ዛፎቹን በማየታቸውና ስማቸውንም በማወቃቸው በጣም ደስተኛ መሆናቸውን ለከድጃ አባት ነግረው የዛፎቹን ስም ስለነገሯቸው አመስገኗቸው፡፡ ከዚያም ከድጃና ጓደኞቿ ከዛፎች ስር ተቀምጠው ቅልብልቦሽ ሲጫወቱ ካመሹ በኋላ ከድጃ ወደ ቤታቸው ሸኘቻቸውና ሄዱ።

**ጥያቄዎች**

1. ከድጃ ስንት ጓደኞች አሏት? ስማቸውስ ማን ይባላል?
2. ከድጃና ጓደኞች ከነከድጃ ቤት ጓሮ ምን አዩ?
3. የከድጃ ጓደኞች የከድጃን አባት ምን ጠየቋቸው?
4. የዛፎቹ ስም ምን ይባላል?
5. ከድጃና ጓደኞቹ ከዛፎቹ ሥር ተቀምጠው ምን አደረጉ?

**ምክር** ፡- ልጆች በእናንተም አካባቢ ብዙ የተለያዩ ዛፎች ስለሚኖሩ አዋቂ ሰዎችን እየጠየቃችሁ ስማቸውን መተዋወቅ ይኖርባችኋል፡፡

## 7ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሁለተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች! ልክ ናችሁ። ባለፈው ዕለት ከድጃና ጓደኞቿ እነ ከድጃ ቤት ከከድጃ ጋር ሊጫወቱ ሄደው የሚያማምሩ ሦስት ዛፎችን አይተው እንደተደሰቱና የዛፎቹንም ስም የከድጃን አባት አቶ መሐመድን ጠይቀው እንደነገሯቸው ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ከድጃና ጓደኞቿ በአካባቢያቸው የሚገኙት ዛፎችን እንዴት እንደሚንከባከቧቸው እንሰማለን፡፡

ከድጃ በቤታቸው ጓሮ ያሉትን ሦስቱን ዛፎች በጣም እየወደደቻቸው መጥታለች፡፡ አዘውትራ እየሄደች ዛፎቹን ውሃ በማጠጣት አፈር በማስታቀፍ መንከባከብ ጀምራለች፡፡ ያላስፈላጊ የበቀሉ አረሞችን እየነቀለች ትጥላለች፡፡ አንድ ቀን ከድጃ ከሳድያ እና፣ ከነኢማ ጋር አብራ ለመጫወት ፈለገችና ወደ ጓደኞቿ ቤት በመሄድ ጠርታቸው መጣችና ከነዚያ ከሚወዷቸው ሦስቱ ዛፎች ሥር ተቀምጠው መጫወት ጀመሩ፡፡ እየተጫወቱ ሳለ ሳድያ እነኝህ ዛፎች እንዴት እንዲህ ሊያምሩ ቻሉ? በማለት ከድጃን ጠየቀቻት። ከድጃም ለጓደኞቿ እንዲህ አለቻቸው፤ እነዚህ እኛ ጓሮ ያሉት ዛፎች እኮ እንደዚህ አምረው ያደጉት አባትና እናቴ አዘውትረው እንክብካቤ ስለሚያደርጉላቸው ነው፡፡ ውሃ በማጠጣት፣ አፈር በማስታቀፍ ዘወትር አስፈላጊ እንክብካቤ ስለሚያደርጉላቸው ነው፡፡ እኔም እኮ አሁን ዛፎቹን በመንከባከብ ቤተሰቤን እየረዳሁ ነው፡፡ ግን እኮ ጓደኞቼ አለች ከድጃ እንደነዚህ እኛ ግቢ እንዳሉት ዛፎች በአካባቢያችንም ሌሎች ብዙ ዛፎች አሉ፡፡ ለምን በእረፍት ቀናችን በአካባቢያችን የሚገኙትን ዛፎች ውሃ በማጠጣት፣ አፈር በማስታቀፍና አረም በመንቀል አንንከባከባቸውም? ብላ ጓደኞቿን ጠየቀቻቸው፡፡ እኛ እኮ በደንብ ብንከባከባቸው አካባቢያችንን ያሳምረዋል፣ ለመድሃኒት የሚሆኑም ብዙ ዛፎች ስላሉ ለአካባቢያችን ማህበረሰብ በብዙ መልኩ ይጠቅማሉ፡፡ ለቤት መሥሪያ፣ ለማገዶም ይጠቅማሉ፡፡ ስለዚህ ብንከባከባቸው ምን ይመስላችኋል? አለቻቸው፡፡ አንዳንዶቹን ዛፎች አይታችኋቸዋል? በቂ እንክብካቤ ስላላገኙ እየደረቁ ነው፡፡ ስለዚህ እረፍታችን በሆነ ጊዜ ብንከባከባቸው ከመድረቅ ይድናሉ አለች፡፡ ጓደኞቿም ከድጃ ባቀረበችው ሃሣብ ተስማምተው ከዚያን ዕለት ጀምረው በአካባቢያቸው የሚገኙትን ዛፎች መንከባከብ ጀመሩ፡፡ ዛፎቹም በቂ እንክብካቤ ስላገኙ እያማሩ ሄዱ፡፡ የከድጃ አባትና እንዲሁም ሌሎችም የአካባቢው ሰዎች ልጆቹን በጣም አመሰገኗቸው፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ከድጃ በጓሯቸው ለሚገኙት ዛፎች ምን ታደርግላቸዋለች?
2. ከድጃ ጓደኞቿን ጠርታ ምን ነገረቻቸው?
3. ከድጃና ጓደኞቿ በአካባቢያቸው ያሉትን ዛፎች ሲንከባከቡ ሌላ ማን እገዛ አደረገላቸው?
4. ከድጃና ጓደኞቿ በአካባቢያቸው ለሚገኙ ዛፎች እንክብካቤ ማድረጋቸው ለአካባቢያቸው የሚሰጠውን ጥቅም ምንድን ነው?

**ምክር**፡-እናንተም ልጆች እንደ ከድጃና ጓደኞቿ በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ዛፎች አስፈላጊውን ሁሉ ነገር በማድረግ መንከባከብ አለባችሁ፡፡ ዛፎች ሲያድጉ ደግሞ አካባቢያችሁን ያስውባሉ፡፡ ለተለያዩ ነገሮችም ይጠቅማሉ፡፡ ስለዚህ አዘውትራችሁ ተንከባከቧቸው፡፡ እሺ፡፡

## 7ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሦስተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች! ልክ ናችሁ። ባለፈው ዕለት ከድጃና ጓደኞቿ በአካባቢያቸው የሚገኙትን ዛፎች እንዴት እንደተንከባከቧቸው ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለ ከድጃና ስለ ሁለቱ ትንንሽ ተክሎች እንሰማለን፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ከድጃ ከእናቷ ከወይዘሮ ቀመርያ ጋር አጎቷ አቶ ሳላዲንን ሊጠይቋቸው ሄዱ፡፡ አጎቷ ቤት እንደደረሱም ከድጃ አጎቷን፣ የጎቷን ባለቤትና ያጎቷን ልጆች አገኘቻቸውና በጣም ደስ አላት። የከድጃ እናት ከአቶ ሳላዲንና ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ሃይሻ ጋር ቁጭ ብለው መጫወት ጀመሩ። ከድጃም ካጎቶቿ ልጆች ከፋጡማና፣ ከሳዲያ ጋር አባሮሽና ድብብቆሽ መጫወት ጀመረች፡፡ ብዙ ከተጫወቱ በኋላ ደከማቸውና ጥላ ፈልገው የማንጎው ዛፍ ስር ቁጭ አሉና ተረት እያወሩ መጫወት ጀመሩ፡፡ ተረቱን አውርተው ከጨረሱ በኋላ በግቢ ውስጥ ወዳሉት ተክሎች ደግሞ እየተዟዟሩ መመልከት ጀመሩ። ታዲያ ከድጃ ሁለት የሚያማምሩ ትንንሽ ተክሎች አየችና ውይ ሲያምሩ! ስማቸው ማን ይባላል? ብላ ፋጡማን ጠየቀቻት፡፡ ፋጡማም ይኸኛው የእንጆሪ ተክል ሲሆን ይኸኛው ደግሞ፣ የኮሽም ተክል ነው አለቻት። ሲያድጉም ፍሬ ያወጣሉ የሁለቱም ፍሬ ይበላል አለቻት፡፡ ነገር ግን አድገው ፍሬ እንዲሰጡ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። እኛም ሆን አባታችንና እናታችን ሁሌ እንንከባከባቸዋለን፡፡ በየጊዜው ውሃ እናጠጣቸዋለን፣ አረም እንነቅልላቸዋለን። ስለዚህ እንደዚህ አምሮባቸው ይታያሉ አለች ፋጡማ፡፡ ከድጃም እስኪ ከነዚህ ተክሎች ለኔም ስጪኝና እቤት ወስጄ እተክላቸዋለሁ አለቻት። ፋጡማም አሁን ከዚህ ላይ ቆርጬ ብሰጥሽ ይደርቃል፤ የምትፈልጊ ከሆነ ሌላ ግዜ ለአባቴ ነግሬው እሱ ችግኙን ገዝቶልሽ እቤት ድረስ ይዞልሽ ይመጣል አለቻት። ከድጃም እሺ እንዳትረሺ ንገሬሻለሁ አለቻት፡፡ ስማቸውን ማን ማን አልሺኝ? አለቻት፡፡ ፋጡማም እንደዚህ ትረሻለሽ እንዴ! እንግዲያው ልድገምልሽ፤ ይኸኛው ኮሽም፣ ይኸኛው ደግሞ እንጆሪ ይባላሉ አለቻች፡፡ ከድጃም እሺ በይ እኛ ግቢ እንዲኖሩ ስለምፈልግ ከአጎቴ ጋር ይዘሽልኝ እንድትመጪ፤ ብላ ተያይዘው ወደቤት ገቡ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ከድጃ ከእናቷ ጋር ወዴት ነው የሄደችው?
2. የከድጃ የአጎት ልጆች ስም ማን ነው?
3. ከድጃና የአጎቷ ልጆች ምን አደረጉ?
4. በአትክልቶቹ መሃል ሲዘዋወሩ ከድጃ ፋጡማን ምን ጠየቀቻት?
5. ከድጃ የጠየቀቻቸው ተክሎች ስም ምን ይባላል?
6. ከድጃ ፋጡማን ምን ስጪኝ አለቻት? ፋጡማስ ምን አለቻት?
7. መጨረሻ በምን ተስማሙ?

**ምክር**፡- አያችሁ ልጆች በአካባቢያችሁ የሚገኙ ተክሎችን ስማቸውን ጥቅማቸውን በማወቅ አስፈላጊ እንክብካቤ ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡

## 7ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአራተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች! ልክ ናችሁ። ባለፈው ዕለት ከድጃ ከእናቷ ከወይዘሮ ቀመርያ ጋር ወደ አጎቷ አቶ ሰላዲን ቤት ሄዳ ከሁለት ትንንሽ ተክሎች ጋር ተዋውቃ እንደነበር ሰምተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ ዛፎች ለሰው ልጅ የሚሰጡትን ጥቅም እንሰማለን፡፡

ከድጃና ጓደኞቿ በእረፍት ጊዜያቸው አዘውትረው በአካባቢያቸው የሚገኙት ዛፎችን በመጎብኘትና በመንከባከብ ግዜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ አንድ ቀን ሳዲያ "እነዚህ ዛፎች ለሰው ልጆች ምን ምን ዓይነት ጥቅም ይሰጣሉ?" ብላ ከድጃን እና ነኢማንን ጠየቀቻቸው። ነኢማም ፈጠን ብላ "ዛፎች ለሰው ልጅ ብዙ ጥቅም እንደሚሰጡ ሰምቻለሁ፡፡ ነገር ግን ከኛ በበለጠ የዛፎችን ጥቅም እንዲነግሩን ነገ መምህራችንን ብንጠይቃቸው ጥሩ ነው" አለች፡፡ ከዚያም በሚቀጥለው ቀን ወደ ት/ቤት እንደደረሱ መምህራቸውን እባክዎ መምህር አንድ ጥያቄ ልንጠይቅዎት ፈልገናል ብለው ሦስቱ ጓደኛሞች መምህራቸውን ጠየቁ። መምህራቸውም "ደስ ይለኛል ጥያቄአችሁ ምንድን ነው?" አሉ። ከዚያም ከድጃ "ዛፎች ለሰው ልጅ የሚሰጡት ጥቅም እንዲሁም ሰዎች ለዛፎች የሚሰጡት ጥቅም ምንድነው?" ብላ ጠየቀች፡፡ መምህራቸውም "ዛፎች ለሰው ልጅ የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣሉ፡፡ ለምሣሌ፡- አካባቢን ያስውባሉ፣ በክረምት ግዜ አፈር እንዳይሸረሸር ያደርጋሉ፣ ለመድሃኒትነት ይጠቅማሉ፣ ለቤትና ለተለያዩ ነገሮች መሥሪያ ይጠቅማሉ፣ ለእንስሳት መኖሪያ ይጠቅማሉ፣ ለምግብነት ይጠቅማሉ፣ ለማገዶነት ይጠቅማሉ፡፡ ሰዎች ደግሞ ይህንን ሁሉ ጥቅም እንደሚሰጡ ስለሚያውቁ ዛፎችን ይንከባከቧቸዋል፡፡ ውሃ ያጠጧቸዋል፣ አረሞችን እየነቀሉ ይንከባከቧቸዋል፡፡ ስለዚህ ይህንን ስንመለከት ተክሎች ያለሰው፣ ሰው ደግሞ ያለ ተክሎች መኖር ይቸግራቸዋል ማለት ነው" ብለው መምህራቸው ገለፁላቸው። ሦስቱ ጓደኞችም ባገኙት መልስ ተደስተው መምህራቸውን አመስግነው ወደ ክፍል ገቡ፡፡

<u>**ጥያቄዎች**</u>

1. ከድጃና ጓደኞቿ በእረፍት ቀናቸው ወዴት ሄዱ?
2. ከድጃና ጓደኞቿ አስተማሪያቸውን ስለምን ጠይቋቸው?
3. የከድጃ አስተማሪ ለነከድጃ ምን ነገሯቸው?
4. ተክሎች ለሰው ልጅ የሚሰጡት ጥቅም ምንድን ነው?
5. ሰው ለተክሎች የሚያደርገው እንክብካቤ ምንድን ነው?
6. ተክሎችን ባንንከባከብ ምን የሚገጥመን ይመስላችኋል?

<u>**ምክር**</u>፡- አያችሁ ልጆች ዛፎች (ተክሎች) ለሰው ልጅ ጠቃሚዎች ናቸው ሰውም ለተክሎች ጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህ ተክሎችን በጋራ መንከባከብ ያስፈልጋል እናንተም ይህንን ተረድታችሁ ተክሎችን በሚገባ ተንከባከቡ፣ ስለማታወቋቸው የዛፍ አይነቶች ደግሞ ጠይቃችሁ ጥቅማቸውን መረዳት ይኖርባችኋል፡፡ እሺ፡፡

## 7ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአምስተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች! ልክ ናችሁ። ባለፈው ዕለት የዛፎችንና ለሰው ልጅ የሚሰጡትን ጥቅም ምን እንደሆነ ሰምተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለጓሮ አትክልቶች እንሰማለን፡፡

ከድጃና ጓደኞቿ በእረፍት ጊዜያቸው አዘውትረው በአካባቢያቸው የሚገኙት ዛፎችን በመጎብኘትና በመንከባከብ ግዜያቸውን ያሳልፉ ነበር፡፡ አንድ ቀን ከድጃ እና ነኢማ ወደ እነሳዲያ ግቢ ኳሳቸውን ይዘው ለመጫወት ገቡ። ኳሷን እየወረወሩ ሲጫወቱ ኳሷ ከቤቱ በስተጀርባ ካለው አትክልት መካከል ላይ ወደቀች። ኳሷን ለማንሳት እየተሯሯጡ ሲሄዱ የነኢማ ታላቅ ወንድም አክመል ድምፁን ጎላ አድርጎ "ነግሬአችኋለሁ! አትክልቶቼን እንዳትረግጡ። ኳሷን ፍለጋ ከሆነ ቀስ ብላችሁ በመደቡ መካከል ባለው ቦይ አልፋችሁ መሄድ ትችላላችሁ" አላቸው። እነከድጃም መሮጣቸውን ትተው ቆም አሉ። ሳድያም "አክመል አይዞህ እኛ ምንም ለማበላሸት አንፈልግም። ከፈቀድክልንም ልናግዝህ እንችላለን። ነገር ግን ምን እንደምንረዳህ ንገረን" አለችው። ነኢማና ከድጃም "አዎ ልናግዝህ እንችላለን። በዚያውም የእያንዳንዳቸውን ተክል ስም እንድትነግረን እንፈልጋለን አሉት። አክመልም "የምትረዱኝ እንኳ ለጊዜው የለም። ኳሳችሁን ደግሞ እኔ አነሳላችኋለሁ" አላቸው። እነከድጃም "የአትክልቶቹ ስምስ ማን ይባላል?" አሉት እሱም በመስመር በመስመር የተተከሉትን የጓሮ አትክልት ዓይነቶች በእጁ እየጠቆመ ይነግራቸው ጀመር። በነዚህ ሁለት መስመሮች ያለው ካሮት ነው። በነኝህ ሦስት መስመሮች ደግሞ ያለው ቲማቲም ነው። ይህ በመካከል ያለው አንድ መስመር ደግሞ ሰላጣ ነው። ቶሎ የሚደርስና በአጭር ጊዜ የሚነቀል ነው። እነኝህ አራት መስመሮች ደግሞ የጥቅል ጎመን ችግኞች ናቸው። ወደዚህ ካዛወርኳቸው ገና አንድ ሳምንት ነው። አምስቱ መስመሮች ደግሞ የቃሪያ ናቸው። እነኝህ ስድስቱ መስመሮች የቆስጣ ሲሆኑ እነኝህ ሁለቱ ደግሞ የጎመን ናቸው። እንደምታዩት ጎመኑ ለመቆረጥ የደረሰ ነው። እነኝህ ሁሉ የጓሮ አትክልት ይባላሉ። እነኝህን መመገብ ለጤና በጣም ተስማሚ ነው። በጥሩ ሁኔታ ስለተንከባከብኳቸው እንደምታዩአቸው ያምራሉ። ነኢማም "አንተ ከነዚህ አትክልቶች ምን ጥቅም ታገኛለህ? አለችው። አየሽ ነኢማ አትክልቶቹ ሲደርሱ ከቤት ፍጆታ አልፈው ምርቱን ስሸጥ ገቢ ያስገኝልኛል" አላቸው። እነከድጃም አክመልን አመስግነው ኳሷን ተቀብለውት ወደጨዋታቸው ሄዱ።

<u>**ጥያቄዎች**</u>

1. ከድጃ እና ነኢማ ወደ እነሳዲያ ግቢ ለምን ገቡ?
2. የነኢማ ታላቅ ወንድም አክመል ድምፁን ጎላ አድርጎ ምን አላቸው?
3. እነሳድያ ግቢ የነበሩት የጓሮ አትክልቶች ምን ምን ናቸው?
4. ከሁሉም የጓሮ አትክልቶች ብዙ መስመሮቸ ያሉት የትኛው ነው?
5. የትኛው የጓሮ አትክልት ለመቆረጥ የደረሰ ነበር?
6. የጓሮ አትክልትን መመገብ ለምን ይጠቀማል?
7. አክመል ከጓሮ አትክልቱ ምን ጥቅም ያገኛል ትላላቸሁ?

<u>**ምክር**</u>፡- አያችሁ ልጆች የጓሮ አትክልቶች ለሰው ልጅ እጅግ ጠቃሚዎች ናቸው። ስለዚህ የጓሮ አትክልቶችን መንከባከብ ይገባቸዋል።

# 8ኛ ሳምንት

## "ከዕለታት አንድ ቀን"

## 8ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአንደኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ሳምንት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች፣ ልክ ናችሁ። ባለፈው ሣምንት ዛፎችና የጓሮ አትክልቶች ስለሚሰጡት ጥቅም ሰምተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ አብዲና ኢብራሂም ጠዋት፣ ቀን፣ ማታ እና ሌሊት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንደተዋወቋቸው እንሰማለን።

ከዕለታት አንድ ቀን አብዲና ኢብራሂም ለጉብኝት ኢንዚ ውስጥ ወደሚገኝ አንድ አፀደ ሕፃናት ከመምህራቸው ጋር ሄዱ እንደደረሱም ወደ አንድ የሕፃናት ክፍል ገቡ፡፡ ሕፃናቱ በሙሉ ቁጭ ብለዋል፡፡ መምህራቸው ጠዋት፣ ቀን፣ ማታ እና ሌሊት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለሕፃናቱ ገለፃ እያደረገች ነበር፡፡ አብዲና ኢብራሂም እነዚህን ቃላቶች ሲሰሙ ተደሰቱ፡፡ የሕፃናቱ መምህርት ትምህርቱን በመቀጠል "ልጆች ጠዋት ከእንቅልፋችሁ ተነስታችሁ ፊታችሁን ታጥባችሁ፣ ቁርሳችሁን በልታችሁ ደብተራችሁን ይዛችሁ ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ እስከ ምሣ ሰዓት ድረስ ትማራላችሁ አይደል? ይህ ጊዜ ጠዋት ይባላል፡፡ ከምሳ ሰዓት በኋላ እስከሚመሽ ድረስ ደግሞ ከሰዓት በኋላ ይባላል፡፡ ማታ የምንለው ደግሞ ሁሉም ሰው ከሥራው ወይም ከትምህርት ቤት ሲመለስና ሲመሽ ነው። ሁሉም መኝታ ውስጥ ገብቶ ሲተኛ ሌሊት ይሆናል" አለች፡፡ ኢብራሂም እጁን አውጥቶ "መምህርት ጨለማ የሚሆነው መቼ ነው? በዚያ ጊዜ የሚታይ ነገርስ አለ?" በማለት ጠየቀ። መምህርቷም "ጠዋትና ቀን ሲሆን ፀሐያማ ነው፡፡ ምሽትና ሌሊት ሲሆን ደግሞ ጨለማ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በምሽት ጊዜ በሰማይ ላይ ጨረቃና ኮከብ ይታያሉ" አለች፡፡ አብዲና ኢብራሂምም በሰሙትና ባወቁት ነገር ተደሰቱ። ዛሬ እዚህ የሰማነውን ለጓደኞቻችን መንገር አለብን ተባባሉ፡፡ በዚሁ ጉብኝታቸውን ጨርሰው ከመምህራቸው ጋር ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. የሰማችሁት ተረት ስለምን የሚያወራ ነበር?
2. ለጉብኝት ሌላ አፀደ ሕፃናት የሄዱት እነማን ነበሩ?
3. አፀደ ሕፃናቱ እንደደረሱ የትኛው ክፍል ገቡ?
4. ጠዋት ምን ምን ይደረጋል?
5. ጠዋትና ቀን ሲሆን ምን ትታያለች?
6. ሌሊት ላይ ምን ይሆናል?
7. ምሽትና ሌሊት ሲሆን ምን ይታያል?

**ምክር**፡- ልጆች እናንተምጠዋት፣ ቀን፣ ማታና፣ ሌሊትየሚለውን ጊዜን ገላጭ ቃላት ማወቅ አለባችሁ፡፡ ስለዚህ በደንብ ልዩነታቸውን እወቁ እሺ፡፡

## 8ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሁለተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች፤ ልክ ናችሁ። ባለፈው ቀን ጠዋት፣ ቀን፣ ማታ እና ሌሊት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሰምተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ ሕፃናቱ የዱር እንስሳትን እንዴት እንደተዋወቋቸው እንሠማለን፡፡

የኢንዚ አፀደ ህፃናት መምህርት የሆነችው መምህርት ቀመርያ የክፍሉን ሕፃናት በሙሉ የእንስሳቶች መኖሪያን ለማሳየት አሰበች፡፡ ጥዋት ወደ ክፍል እንዳገባች ለሕፃናቱ "ልጆች ነገ ሁላችንም የእንስሳቶች መኖሪያን ሄደን እንጎበኛለን" አለቻቸው ፡፡ በማግስቱ ልጆቹ በጠዋት ተነስተው ወደ መምህራቸው ሄዱ። መምህርቷም "ልጆች! በጉብኝታችን ወቅት ወዲህና ወዲህ መሯሯጥ የለባችሁም። ለብቻ ተነጥላችሁም መንቀሳቀስ አይቻልም። ስለዚህ ሁላችሁም ከኔ ጋር ሆናችሁ ነው ጉብኝቱን የምናካሂደው እሺ!። በሉ አሁን ወደዚያው እንሂድ!" ብላ ጉዞአቸውን በአንድ ላይ ጀመሩ። እንደደረሱም የተለያዩ የዱር እንስሳቶችን በወንፊት ሽቦ ተከልለው ተመለከቱ። አንበሳ፣ ጦጣ፣ ዝንጀሮ፣ ጅብ፣ ሚዳቋ፣ ከርከሮና ሰስ የመሳሰሉት ነበሩ። የእያንዳንዱንም እንስሳ ስም መምህራቸው ነገረቻቸው። ከዚያም ጉብኝታቸውን ተመለሱና ወደ ት/ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ወደቤት የመመለሻ ሰዓት ደርሶ ስለነበር መምህራቸው "ልጆች አሁን ወደቤታችሁ ሂዱ በጉብኝታችን ስላየነው ሁሉ ነገ እንወያያለን" አለቻቸው። በሚቀጥለው ቀን መምህር ቀመርያ ወደ ክፍል ገብታ ከህፃናቱ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ "ልጆች <u>ትናንትና</u> የት ሄደን ነበር?" ብላ ጠየቀቻቸው። ሕፃናቱም ስለሄዱበት ቦታ አንድ በአንድ ነገሯት። መምህርቷም "<u>ዛሬ</u> ደግሞ ወረቀት እሰጣችሁና ካያችኋቸው የዱር እንስሳት ደስ ያላችሁን ትስላላችሁ" አለቻቸው፡፡ ከዚያም ሕፃናቱ የወደዱትን ስለው ጨረሱ፡፡ መምህር ቀመርያም እየዞረች በማየት የህፃናቱን ሥዕል አደነቀች፡፡ በመጨረሻም "<u>ነገ</u> ደግሞ የሳላችሁትን ሥዕሎች ከለር እንቀባለን እሺ" አለቻቸውና ወደ የቤታቸው ሂዱ፡፡

**<u>ጥያቄዎች</u>**

1. መምህር ቀመርያ ሕፃናቱን ይዛ የት ሄደች?
2. በእንስሳቱ መኖሪያ ውስጥ ምን ምን ዓይነት እንስሳት አዩ?
3. መምህር ቀመርያ ከጉብኝቱ በኋላ በክፍሉ ውስጥ ሕፃናቱን ምን ጠየቀቻቸው?
4. መምህሯ በክፍል ውስጥ ሕፃናቱን ምን አሠራቻቸው?
5. ሕፃናቱ ሥዕሉን ሠርተው ሲጨርስ መምህር ቀመሪያ ምን አለቻቸው?

**<u>ምክር</u>**፡-ልጆች ሁልግዜ ስለምታያቸው ስለምትሰሚቸው ነገሮች አስተውሎ በማየት ማድነቅ በምትጠየቁበት ጊዜ በቃልም በፀሐይም በሥዕልም መግለጽ መቻል አለባችሁ እሺ፡፡

## 8ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለሦስተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች፣ ልክ ናችሁ። ባለፈው ዕለት መምህር ቀመርያ ሕፃናቱን የእንስሳት መኖሪያን አስጎብኝታ በክፍል ውስጥ ካየችው የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደጠየቀች ሰምተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ መምህርት ቀመርያ የሣምንቱ ቀናትን ለሕፃናቱ እንዴት እንዳስተዋወቀች እንሰማለን፡፡

መምህርት ቀመርያ ሁል ጊዜ ስትሄድም ስትቀመጥም አልጋዋ ላይ ጋደም ስትልም የሳምንቱ ቀናት እነማን ናቸው? ልጆች ልጆች እንወቃቸው የሚለውን መዝሙር መዘመር ትወዳለች፡፡ አንድ ቀን ልጆቹን እስኪ የምትወዱትን መዝሙር ንገሩኝ እኔ ደግሞ በጣም የምወደውን መዝሙር እነግራችኋላሁ ብላ ጠየቀች፡፡ ሕፃናቱም በየተራ የሚወዱትን መዝሙር ነገሯት፡፡ ከዚያ እሷም እኔም በጣም የምወደው መዝሙር ልጆች የቱ መሰላችሁ የሣምንቱ ቀናት የሚለውን መዝሙር ነው አለቻቸው፡፡ ከዚያም የምወደው ለምን መሰላችሁ አለቻቸው፡፡ የሣምንቱ ቀናቶችን ስም ያስተዋውቀኛል፡፡ በሣምንት ውስጥ ስንት ቀናት እንዳለ ይነግረኛል አለቻቸው። ልጆች የሣምንቱ ቀናት እነማን እንደሆኑ ታውቃላችሁ፡፡ ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ሐሙስ፣ ዓርብ፣ ቅዳሜ፣ እሁድ ይባላሉ፡፡ ከነዚህ ቀናቶች ውስጥ ከሰኞ እስከ ዓርብ የትምህርትና የሥራ ቀናት ናቸው፡፡ ቅዳሜና እሁድ ደግሞ የእረፍት ቀናት ናቸው፡፡ አንድ ሣምንት ሰባት ቀናቶች አሉት፡፡ ስለዚህ ይህ መዝሙር የሣምንቱ ቀናትን ስለሚያስተዋውቀኝ በጣም እወደዋለሁ፡፡ አሁን ደግሞ እስኪ እናንተ ንገሩኝ የሣምንቱ ቀናት እነማን ናቸው? ብላ ጠየቀችና ልጆቹ ሁሉም ነገሯት። አሁን ደግሞ የሣምንቱ ቀናት የሚለውን መዝሙር አብረን እንዘምር ብላ መዝሙሩን ጮክ ብለው አብረው ዘመሩ። መምህረቷም ሕፃናቱን አመስግና የዕለቱን ትምህርት ጨረሰች፡፡

**<u>ጥያቄዎች</u>**

1. መምህርት ቀመርያ የምትወደው ምንድነው?
2. የሣምንቱ ቀናትስንትናቸው? ስማቸውስ ምን ይባላል?
3. የትምህርት ቀናት ከመቼ እስከ መቼ ነው?
4. የእረፍት ቀናቶች እነማን ናቸው?
5. እናንተ በእረፍት ቀናችሁ ቅዳሜና እሁድ ምን ታደርጋላችሁ?

**<u>ምክር</u>**፡-ልጆች የሣምንቱ ቀናትን ስም ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህእናንተም የሣምንቱ ቀናቶችን እስከ ስማቸው በደንብእወቁ እሺ፡፡

## «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአራተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች፣ ልክ ናችሁ። ባለፈው ዕለት መምህር ቀመርያ የሣምንቱ ቀናትን ለሕፃናቱ እንዴት እንዳስተዋወቀች ሰምተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ የሣምንቱ ቀናትና ወራቶች ያላቸውን ግንኙነት መምህርት ቀመርያ ለሕፃናቱ እንዴት እንዳስተዋወቀች እንሰማለን፡፡

መምህር ቀመርያ ቀይ ቆንጆ የሚያምር ቀሚስ ለብሳለች፡፡ በላዩ ላይ የሚያምር ጥቁር ኮት ደርባለች፡፡ ዛሬ በጣም ደስተኛ ሆናለች፡፡ ትስቃለች፡፡ ሁሉንት የኢነዚ አፀደ ሕፃናትና ሠራተኞችን በሙሉ እየሳመች ትጨብጣለች፡፡ ታዲያ ይህንን ያስተዋለችው ጓደኛዋ መምህርት ዘሃራ "ምነው ቀመርያ ዛሬ በጣም አምሮብሻል፡፡ ደግሞም በጣም ደስተኛ ሆነሻል፡፡ ምነው ምን አገኘሽ?" አለቻት፡፡ መምህር ቀመርያም "አዎ ዘሃራ ልክነሽ ዛሬ የተወለድኩበት ቀን ሰለሆነ በጣም ደስተኛ ነኝ።" ብላት ወደ ክፍሏ ገባችና ሕፃናቱን በደስታ ሰላምታ ሰጠቻቸው፡፡ እነሱም ሰላም አሏት፡፡ "ልጆች! ዛሬ የተወለድኩበት ቀን ነው፡፡ ወሩ ማን መሰላችሁ? ግንቦት ነው። ግንቦት 21 ቀን ሁሌ የኔ ልደት ነው፡፡ ባለፈው ትምህርታችን የሣምንቱ ቀናትን ተዋውቀናል አይደል ልጆች" ብላ ስትል ሁሉም በአንድነት "አዎ!" ብለው መለሱ፡፡ አዎ ወር የሚባለው 30 ቀን ይይዛል፡፡ እኔም ልደቴ በግንቦት ወር ነው፡፡ ታዲያ ከሠላሳ ቀናቱ ውስጥ ሃያ ሁለቱ ቀናት የሥራ ሲሆን ስምንቱ ቀናት ደግሞ የዕረፍት ቀናት ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ ሣምንት ሰባት ቀናት እንዳሉት አውቀናል፡፡ አንድ ወር ደግሞ አራቱ ሣምንት በአንድ ላይ ተደምሮ የሚገኝ ውጤት ነው፡፡" አለችና "ቅድም እንዳልኳችሁ ዛሬ የኔ ልደት ስለሆነ ያመጣሁላችሁን ጣፋጭ ከረሜላዎች አብረን እንበላለን" አለቻቸውና አብረው በሉ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. መምህር ቀመርያ የለበሰችው ልብስ ምን ዓይነት ነበር?
2. ለምን መምህር ቀመርያ ደስተኛ ሆነች?
3. በክፍል ውስጥ ለሕፃናቱ መምህር ቀመርያ ምን ነገረቻቸው?
4. የመምህር ቀመርያ የተወለደችው በየትኛው ወርና በየትኛው ቀን ነው?
5. ወር ማለት ምን ማለት ነው?
6. ወር ስንት ቀናት አሉት?
7. በወር ውስጥ ስንት የሥራ ቀናት ስንት የእረፍት ቀናት አሉ?

**ምክር**፡-ሁል ጊዜ ወር የሚባለው አራት ሣምንት እንደሚይዝና 30 ቀናት፣ 22 ቀን የትምህርት ቀን ሲሆን ስምንቱ ደግሞ የእረፍት ቀን መሆኑን እወቁ እሺ፡፡ በእለት ተእለት ሕይወታችሁ ገጠመኝ ጋር የተያያዘ እንደሆነ እወቁ እሺ፡፡

## 8ኛ ሳምንት

### «ከዕለታት አንድ ቀን» (የተረት ጊዜ ለአምስተኛው ቀን)

ልጆች ባለፈው ዕለት የሰማነው ተረት ስለምን የሚገልጽ ነበር? ማን ያስታውሳል? ጎበዞች፣ ልክ ናችሁ። ባለፈው ዕለት ስለ መምህርት ቀመርያ የልደት ቀን ሰምተን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ መምህርት ቀመርያ ስለ ወራትና ዓመት ግንኙነት እንዴት ለኢብራሂምና ለአብዲ እንነገረቻቸው እንሰማለን፡፡

ኢብራሂምና አብዲ በኢንዚ ውስጥ ባለው አፀደ ሕፃናት ይማራሉ፡፡ አንድ ቀን በሠፈራቸው ሜዳ ላይ ቁጭ ብለው እየተጫወቱ ስለነበር በረዳቸው፡፡ ዝናብ ሊመጣ ነው መሰለኝ መቀዝቀዝ ጀመረ አለ አብዲ፡፡ ኢብራሂም ደግሞ አሁን እኮ ስለመሸ ነው የበረደህ አለው፡፡ ግን ዝናብ በጣም የሚበዛው መቼ ነው ብሎ አብዲ ኢብራሂምን ጠየቀው፡፡ ይህንን እኔ አላውቅም እስኪ ነገ ጠዋት መምህርት ቀመርያን እንጠይቃታለን ተባብለው ወደየቤታቸው ሄዱ፡፡ በማግስቱ ጠዋት አፀደ ሕፃናት እንደደረሱ መምህርት ቀመርያን አገኟትና ጠየቋት፡፡ እሷም እንዲህ በማለት ነገረቻቸው፡፡ ባለፈው ቀን የሣምንቱ ቀናትንና የግንቦትን ወር ልደቴን ምክንያት አድርጌ ነግሬያችሁ ነበር፡፡ ምን መሰላችሁ ወራቶች አሥራ ሦስት ናቸው፡፡ አሥራ ሦስት ወራቶች በአንድ ላይ አንድ ዓመት ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነሱም መስከረም፣ ጥቅምት፣ ሕዳር፣ ታህሣስ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዝያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴ፣ ጳጉሜን ተብለው ይጠራሉ፡፡ ጳጉሜን በኛ ሀገር ብቻ የሚገኝ ወር ነው፡፡ አንዳንዴ አምስት ቀን አንዳንዴ ስድስት ቀን ይሆናል፡፡ አስሩ ወራት ፀሐያማ ሲሆኑ በጋ በመባል ይጠራሉ፡፡ በጋ የሚባሉት ከመስከረም እስከ ሰኔ ያለው ወር ሲሆን ከሐምሌ እስከ ጳጉሜ ክረምት ይባላል፡፡ በነዚህ ወራቶች የዝናብ ጊዜ ነው፡፡ ለተማሪዎች የእረፍት ጊዜ ነው፡፡ በማለት መምህርት ቀመርያ ለኢብራሂምና ለአብዲ ነገረቻቸው፡፡ እነሱም ባገኙት መልስ ተደስተው መምህራቸውን አመስግነው ወደ ክፍል ገቡ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. ኢብራሂምና አብዲ ሜዳ ላይ ቁጭ ብለው ስለምን ተጨዋወቱ?
2. ኢብራሂምና አብዲ መምህር ቀመርያን ምን ጥያቄ ጠየቋት?
3. መምህር ቀመርያ ለኢብራሂምና አብዲ ጥያቄ ምን መልስ ሰጠቻቸው?
4. ዓመት ስንትወራትአሉት?
5. በጋ ከመቼ እስከ መቼ ድረስ ነው?
6. ክረምት ከየትኛው ወር እስከ የትኛው ወር ድረስ ነው?
7. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኘው ወር የትኛው ነው?

**ምክር**፡- በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችሁ ሂደት ውስጥ ስለሚያጋጥማችሁ የሣምንት፣ የወራት፣ የዓመት ልዩነትናግንኙነት ማወቅ አለበችሁ፡፡ እናንተም ልክ እንደ ኢብራሂናአብዲ መምህራችሁንም፣ ወላጆቻችሁንም እየጠየቃችሁ በደንብ እወቋቸው እሺ፡፡